# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 028 መስከረም 28 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ - ዳኜ አበራ

# የኢሬቻ በዓል

## በቢሾፍቱ ሆረ ሀርሰዴ በድምቀት ተከበረ

### - በዓሉ ኢትዮጵያዊ አንድነትና ወንድማማችነት የታየበት እንደነበርም ተገልጿል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- የኢሬቻ በዓል ትናንት በቢሾፍቱ ከተማ ሆረ ሀርሰዴ በድምቀት ተከብሮ ውሏል፡፡ በሥነሥርዓቱ ላይ የታደሙ እንግዶችም በዓሉ ኢትዮጵያዊ አንድነትንና ወንድማማችነት በጉልህ የታየበት እንደነበር ገልጸዋል፡፡

የኦሮሞ ገዳ ሥርዓት አካል የሆነው የኢሬቻ በዓል ትናንት በቢሾፍቱ ሆረ ሀርሰዴ በአባ ገዳዎችና ሀደ ሲንቄዎች ተባርኮ የተጀመረ ሲሆን፤ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችና የውጭ ሀገር ዜጎች በበዓሉ ላይ ታድመዋል፡፡

ታዳሚዎችም በጭፈራና በኅብረ ዝማሬ ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ በዓሉን ያደመቁት ሲሆን፤ እንግዶችም በዓሉ ልዩ ድባብ ተላብሶ በወንድማማችና በፍቅር መከበሩን ተናግረዋል፡፡

የኢሬቻ በዓል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ገበዮ ገብሬ

አቶ ጥበቡ ታደሰ

## ኮሚሽኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር ስኬታማ ውይይት አካሂዷል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ከመንግሥት፣ ከወጣቶች እና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ስኬታማ ውይይት ማከናወኑን አስታወቀ።

የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ቃል አቀባይ አቶ ጥበቡ ታደሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ኮሚሽኑ ከዚህ በፊት ከመምህራን፣ ከሃይማኖት አባቶች፣ ከሀገር ሽማግሌዎች፣ ከአካል ጉዳተኞች፣ ከወጣቶች እና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት አድርጓል። አሁን ደግሞ ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) እና ከከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች ጋር ውይይት አድርጓል።

ኮሚሽኑ ከባለድርሻ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ብሔራዊ መግባባት ለመፍጠር ሀገራዊ እሴቶቻችንን እንዴት እንጠቀምባቸው?

ገጽ 4

## ኢሬቻ እሴቱን ጠብቆ እንዲከበር ሳደረጉ አካላት የኦሮሚያ ክልል ምስጋና አቀረበ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- የኦሮሚያ ክልል የሆረ ፊንፊኔና የሆረ ሀርሰዴ የኢሬቻ ክብረ በዓል እሴቱን ጠብቆ እንዲከበር አስተዋጽኦ ላበረከቱት አካላት ምስጋና አቀረበ።

በክብረ በዓሉ የታደሙ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም የጎረቤት ሀገራት ተወካዮች ለኦሮሞ ሕዝብ ላሳዩት ወድማማችነትም የላቀ ምስጋና አቅርበዋል፡፡

አከባበሩን አስመልክተው ዛሬ ለሚዲያዎች መግለጫ የሰጡት የክልሉ ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ አቶ ኃይሉ አዱኛ እንደገለጹት፤ በሃይማኖትና በብሔር ሽፋን ብጥብጥና

ኢሬቻ እሴቱን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ገበዮ ገብሬ

አቶ ኃይሉ አዱኛ
















# ወጣቶች ልዩነትን በንግግር የመፍታት ባህላቸውን ሊያሳድጉ ይገባል

## - የኢሬቻ በዓል ታዳሚ ወጣቶች

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ የተጀመሩ ለውጦችን ውጤታማ ለማድረግ በተለይ ወጣቶች የሃሳብ ልዩነትንና ችግሮችን ለመፍታት የመወያየት ባህልን ማጎልበት እንደሚጠበቅባቸው የኢሬቻ በዓልን በሆራ ፊንፊኔ ሲያከብሩ የነበሩ ወጣቶች ተናገሩ።

ወጣት መስከረም ከበደ በሀዋሳ ከተማ ነዋሪ ስትሆን የሙዚቃ ባለሙያም ነች። ወደ አዲስ አበባ የመጣችው የኢሬቻ በዓል ለማክበር ነው።

በአሁኑ ወቅት ወጣቱ ለኢትዮጵያ ሰላም መጠበቅ ቅድሚያ መስጠት አለበት የምትለው ወጣት መስከረም፤ እያንዳንዱ ወጣት ሁለት ኃላፊነት አለበት ብላለች፡፡

አንደኛው በዚህ ዘመን በሀገሪቱ የተከሰቱ ችግሮች እንዳይባባሱ የድርሻውን መወጣት ሲሆን፤ በሌላ በኩል ነገ ለሚረከባት ሀገር ራሱን ለኃላፊነት ማዘጋጀት አለበት፤ ለዚህ ደግሞ ሌሎች የሚሉትን መስማትና በሃሳብ ከሚለዩት ጋርም ቢሆን ውይይት ማድረግ መለመድ አለበት ትላለች።

ከአዲስ አበባ ከቃሊቲ አካባቢ የመጣው ወጣት መርጋ ሶሬሳ በበኩሉ፤ ወጣቱ በተፈጥሮ ሕግ የነገ ሀገር ተረካቢ መሆኑ የግድ በመሆኑ ለዚህ ትልቅ ኃላፊነት ራሱን ሊያዘጋጅ ይገባል ይላል።

ወጣት መርጋ እንደሚለው በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ሁሉም ሰው የራሱ የሆነ ጥያቄ፣ ፍላጎትና ሃሳብ አለው።


ወጣት መስከረም ከበደ


ወጣት መርጋ ሶርሳ ፤


ወጣት ሰሚራ ተማም


ወጣት ዳግማዊት ደበሌ

ነገር ግን እነዚህ ነገሮች እንዲሟሉለት ሲንቀሳቀስ በተመሳሳይ ሌሎች ዜጎችም የየራሳቸው ጥያቄ እንዳላቸው ሊገነዘብና ሊረዳ ይገባል።

ወጣቶች ለሀገር ግንባታ በፖለቲካ ብቻ ሳይሆን በማኅበራዊ ግንኙነትም ውይይቶችን ማድረግ አለባቸው የምትለው ደግሞ ቡራዩ አካባቢ ነዋሪ የሆነችው ወጣት ሰሚራ ተማም ናት።

እንደ ሀገር በርካታ ችግሮች ያሉ ቢሆንም መነጋገር መወያየት ከቻልን በቀላሉ ሊፈቱ የሚችሉ ናቸው የምትለው ወጣት ሰሚራ፤ ለዚህ ደግሞ በገዳ ሥርዓት ውስጥ ያሉትን ጨምሮ በርካታ ሀገር በቀል እውቀቶችን መጠቀም እንችላለን። ለዚህ ደግሞ ወጣቱ በቅድሚያ ራሱን ዝግጁ ሊያደርግ ይገባል ትላለች።

ወጣት ዳግማዊት ደበሌ በበኩሏ፤ በኢትዮጵያ እየተከሰቱ ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ የኢትዮጵያውያን አቅም በቂ ነው ትላለች።

ከሚያለያዩን በላይ የሚያዋድዱን ነገሮች ይበዛሉ የምትለው ዳግማዊት በአንድ ሀገር ውስጥ ለሚከሰት መልካምም ሆነ ጥሩ ያልሆነ ክስተት የወጣቶች ሚና ከፍተኛ ነው። በመሆኑም ወጣቶች ራሳቸውን ሀገር የሚጠቅም ነገር ላይ ለመስራት ዝግጁ ሊያደርጉ ይገባል ብላለች።

ወጣቶቹ እንዳሉት፤ የመወያየት የመነጋገርና የመደማመጥ ባህልን ማሳደግ ወሳኝ ነው። ለዚህ የሚሆን ደግሞ በገዳ ሥርዓት ውስጥ ያሉትን ጨምሮ በርካታ ሀገር በቀል ሥርዓቶች አሉን። በመሆኑም እነዚህን በመጠቀም በመነጋገርና በመደማመጥ እንዲሁም በመቻቻል ችግሮቻችንን ተሻግረን አንድነታችንን ልናጸና ይገባል።

# የቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራም አበረታች ውጤቶች እየተመዘገቡበት ነው

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- ቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራማችን በጅምር ላይ የሚገኝ ፕሮግራም ቢሆንም ጥሩ ውጤቶችን ያስመዘገብንበት ነው ሲል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ እናትዓለም መለሰ እንደገለጹት፤ ቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራም ጅምር ላይ የሚገኝ ቢሆንም ጥሩ ውጤቶች እየተመዘገቡበት ነው፡፡ የፕሮግራሙ አስፈላጊነት እና የራዕዩ እንዲሁም በአጭር ጊዜ ውስጥ ያስመዘገብናቸው ውጤቶች ስኬታማነት ሀገራዊ እና አህጉራዊ ተሞክሮ ለመሆን በመቻላቸው ተመራጭ እና ብዙዎች ሊማሩበት የሚችል ሆኗል።

የቀዳማይ ልጅነት ልማት ሥራውን እንደ ስትራቴጂክ ፕሮግራም በመውሰድ ሥራውን የሚመራ አካል በከንቲባ ጽህፈት ቤት ተደራጅቶ በመምራት ላይ እንደሚገኝ ያስታወሱት ኃላፊዋ፤ ሁለት ሺህ 500 የወላጆች እና አሳዳጊዎች የምክር አገልግሎት ሠራተኞች ሰልጥነው ወደ ሥራ መግባታቸውን ገልጸዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ እናትዓለም ገለጻ፤ ከ56 በላይ ጤና ጣቢያዎች የቀዳማይ ልጅነት ተኮር የሕፃናት እና ወላጆች ጤና ክብካቤ አገልግሎትን ሙሉ በሙሉ በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ ቀሪዎቹም በመሸጋገር ላይ ናቸው። ሁሉም የጤና ጣቢያዎች ጤና ባለሙያዎች ተገቢውን ሥልጠና አግኝተው የስድስት የፌዴራል ሆስፒታል ባለሙያዎች የሪፈራል አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስችል ሥልጠና ወስደዋል።

ፕሮግራሙ ለዘጠኝ ሺህ 500 ለሚሆኑ የሕፃናት እና ወላጆች የአልሚ ምግብ በማቅረብ ላይ ይገኛል ያሉት



ወይዘሮ እናትዓለም መለሰ

ኃላፊዋ፤ 46 የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ወደ ጨዋታ መር የማስተማር ሥነዘዴ ተሸጋግረዋል፡፡ በሺህ የሚቆጠሩ መምህራን የሠለጠኑ ሲሆን፤ የመማር ማስተማር ሥርዓቱን ለመሸጋገር የሚያስችል የምርምር ፕሮጀክት በመካሄድ ላይ ነው ብለዋል፡፡

በከተማዋ ከ150 በላይ የመጫዎቻ ቦታዎች ለምተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅትም በቀዳማይ ልጅነት ልማት እሳቤዎች የተቃኙ ዘጠኝ አዳዲስ የመጫዎች ቦታዎች የለሙ ሲሆን፤ አምስቱ በግንባታ ላይ፣ 91 በዲዛይን ዝግጅት ላይ ይገኛሉ። በተጨማሪም በመደመር ትውልድ መጽሐፍ ሽያጭ 12 የመጫዎች ሜዳዎች ለምተዋል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ኃላፊዋ አክለውም፤ የሕፃናት መዋያዎችን ለማስፋት በተያዘው እቅድ መሠረትም 152 የተለያዩ ሞዴል ያላቸው መዋያዎች ወደ ሥራ ገብተዋል፡፡ በአሁኑ ወቅትም አጠቃላይ ፕሮግራሙን በምርምር እና ስርጸት የሚመራ የልህቀት ማዕከልን በማደራጀት ወደ ሥራ በማስገባት ላይ እንገኛለን ብለዋል፡፡

# በመዲናዋ እየተሰጠ በሚገኘው ነፃ የሕክምና አገልግሎት ከ112 ሺህ በላይ ነዋሪዎች ተጠቃሚ ሆነዋል

## - በነፃ ሕክምናው ከ28 ሚሊዮን በላይ ብር ወጪ ተደርጓል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ እየሰጠ በሚገኘው የክረምት ነፃ የሕክምና የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ከ112 ሺህ በላይ ነዋሪዎች ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን አስታወቀ፡፡ ለነዋሪዎች በተደረገ የሜዲካል ሕክምና እስካሁን ከ28 ነጥብ አራት ሚሊዮን በላይ ብር ወጪ መደረጉም ተገልጿል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ የሕክምና አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ መልካሙ ጥሩነህ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ከሰኔ ወር ጀምሮ እየሰጠ በሚገኘው የክረምት ነፃ የቅድመ በሽታ የመከላከልና ሕክምና የመስጠት ሥራ 112 ሺህ 624 ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን፤ ለሜዲካል ሕክምናውም እስካሁን ከ28 ነጥብ አራት ሚሊዮን በላይ ብር ወጪ ተደርጓል፡፡

በመዲናዋ «በጎነት ለጤናችን» በሚል መሪ ቃል የክረምት ነፃ የበጎ ፈቃድ የቅድመ በሽታ የመከላከልና ሕክምና የመስጠት ሥራ እየተካሄደ የሚገኝ ሲሆን፤ በዚህም መርሀ-ግብር ለ100 ሺህ ነዋሪዎች አገልግሎቱን ለመስጠት ታቅዶ ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት ለ112 ሺህ 624 ሰዎች እስካሁን መስጠት መቻሉን ገልጸዋል፡፡

በመዲናዋ እየተሰጠ ባለው የክረምት ነፃ የቅድመ በሽታ የመከላከልና መደበኛ የሕክምና አገልግሎት ሥራ ምርመራ ከተደረገላቸው 112 ሺህ 624 ሰዎች ውስጥ 64 ሺህ 826 አዋቂዎች፣ 27 ሺህ 807 የሚሆኑት ሕፃናት ሲሆኑ እናቶችና ወጣቶችም ይገኙበታል ተብሏል፡፡


አቶ መልካሙ ጥሩነህ

በተጨማሪም ምርመራ ከተደረገላቸው 112 ሺህ 624 ሰዎች ውስጥ ሁለት ሺህ 713 የሚሆኑት የተገኙባቸው በሽታዎች መደበኛ ሕክምና እና የባለሙያ ክትትል የሚያስፈልጋቸው በመሆናቸው ወደ ሆስፒታል ተልከው እየታከሙ እንደሚገኙ ተናግረዋል፡፡

በመርሀ ግብሩም 16 ሺህ 500 ባለሙያዎች እየተሳተፉ የሚገኙ ሲሆን፤ የደም ግፊትና ስኳር በሽታ ልየታ፣ የማህጸን በር ካንሰር ምርመራ እና ከአንገት በላይ ሕክምና ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራባቸው የሚገኙ በሽታዎች ናቸው ብለዋል፡፡

በተቋሙ በክረምት ነፃ ቅድመ በሽታ የመከላከልና ሕክምና የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እየተሰጡ የሚገኙ የሕክምናና የባለሙያ ምክሮችን በመደበኛ አገልግሎት ለመስጠትና አጠናክሮ ለማስቀጠል የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ነው ሲሉ አመላክተዋል፡፡

# ቢሮው ለልዩ ፍላጎት ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ አደረገ

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ለልዩ ፍላጎት ተማሪዎች በተለይ ለዓይነ ስውራን የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ አደረገ፡፡

“ተደራሽ፣ አካታችና ፍትሐዊ የትምህርት አገልግሎት ለልዩ ፍላጎት ተማሪዎች” በሚል መሪ ሃሳብ የተበረከተው የትምህርት ቁሳቁስ በተለይ ለዓይነ ስውራን መማሪያ የሚያገለግሉ ብሬል ወረቀት፣ የድምፅ መቅረጫ እና መሰል ቁሳቁሶች ናቸው።

በመርሀ ግብሩ ላይ የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ዘላለም ሙላቱ እንዳሉት፤ ትምህርት ቤት በትክክል ለሁሉም ተደራሽና ፍትሐዊ እንዲሆን እየተሠራ ነው፡፡

የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ከሌሎች በተለየ ሁኔታ መደገፍ እንደሚኖርባቸው የገለጹት ኃላፊው፤ የትምህርት ተቋማት ይህንን ለማድረግ አቅም እንዲያገኙና ተደራሽ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ግብዓት ማሟላት እንደ ትልቅ አቅጣጫ ተወስዶ እየተተገበረ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡


ባለፉት አራት ዓመታት የነበሩ ክፍተቶችን በማሻሻል የአስራ ሁለተኛ፣ የስምንተኛ እና የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ ጥሩ መሻሻሎች እያሳዩ እንደሆነም ጠቅሰዋል፡፡

የትምህርት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ወንድሙ ኡመር በበኩላቸው፤ በተያዘው የበጀት ዓመት ለልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ቁሳቁስ ማደራጃነት የሚውሉ 14 አዳዲስ የሪሶርስ ማዕከላትን ለመገንባት እንደታቀደ ገልጸው፤ በተለይ እያንዳንዱ ዓይነ ስውር ተማሪ የብሬልና መሰል አስፈላጊ ቁሳቁስ በተደራጁት የሪሶርስ ማዕከላት በኩል ስርጭት እንዲደረግ ተመቻችቷል ብለዋል። በዚህ መሰረት የሚደረገው ድጋፍና ትኩረት ተማሪዎች የላቀ ውጤት እንዲያመጡ አስተዋፅኦ ያደርጋልም ብለዋል፡፡

በመሆኑም በተፈጠረው መልካም ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑና ጥሩ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ለተማሪዎች መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች አስፈላጊውን እገዛ ለማድረግ ዝግጁ እንደሆነም ጠቅሰዋል።


ዶክተር ዘላለም ሙላት



ቤታ ፃማቶ (ዶ/ር)

# የትምህርት ባለድርሻዎች ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ እኩል ተሳትፎ ሊያደርጉ ይገባል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የትምህርት ባለድርሻዎች ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ እኩል ተሳትፎ ሊያደርጉ እንደሚገባ በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ የሥነ-ትምህርትና ሥነ-ባህሪ ተመራማሪ ቤታ ፃማቶ(ዶ/ር) ገለጹ።

ዶክተር ቤታ ፃማቶ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ወላጆች፣ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ዩኒቨርሲቲዎች እና የትምህርት ዘርፉን በበላይነት የሚመሩ ተቋማት የዘርፉ ባለድርሻ አካላት ተብለው ይጠራሉ። የትምህርት ባለድርሻዎች የዘርፉን ውጤታማነት ለማሻሻል በሚደረገው ጥረት እኩል ተሳትፎና ትብብር ሊያደርጉ ይገባል።

ትምህርት ለሁሉም ዘርፎች የሰለጠነ የሰው ኃይል የሚያቀርብ ነው። ስለዚህ ዘርፉን በጥንቃቄ መምራት ያስፈልጋል። በዘርፉ ብቁ ዜጋ ለማፍራት ረጅም ጊዜ የሚያስፈልግ በመሆኑ በሚደረገው ሂደት ሙያዊ ምክረ ሃሳቦችና ተግባራት ያስፈልጋሉ ብለዋል።

ዶክተር ቤታ በማስተማር እና በሥነ ትምህርት ሳይንስ ያላቸውን ሰፊ ጥናትና እውቀት በማንሳት፤ ባለድርሻ አካላቱ የትምህርት ፖሊሲዎችን በመቅረጽ፣ ማሻሻያዎችን በመተግበር እና የትምህርት ጥራትን ለሁሉም በማረጋገጥ ረገድ የሚጫወቱት ሚና ወሳኝ መሆኑን ገልጸዋል።

የባለድርሻ አካላት ንቁ ተሳትፎ ውጤታማ የትምህርት ፖሊሲዎችንና ማሻሻያዎችን እንዲሁም ተግባራዊ ለማድረግ ወሳኝ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ቤታ፤ አሁን ላይ ከትምህርት ተቋማት፣ ከመንግሥት፣ ከሲቪል ማኅበራት እና ከግሉ ሴክተር የተውጣጡ የተለያዩ አመለካከቶችን ማካተት በትምህርት ላይ ያሉ ውስብስብ ችግሮችን ለመፍታት ይረዳል ብለዋል።

በመንግሥት እና በግሉ ሴክተር መካከል ያለው ትብብር የትምህርት ዘርፉን ለማሻሻል ያለውን ፋይዳ በአጽንኦት ገልጸው፤ ወላጆችን፣ ተማሪዎችን እና ማኅበረሰቦችን ማሳተፍ የባለቤትነት ስሜትን እና የኃላፊነትን ስሜት ያሳድጋል። ይህም የተሻሻሉ የትምህርት ውጤቶችን እና የላቀ የኅብረተሰብ ተሳትፎን እንደሚያመጣ ተናግረዋል።

ወቅቱ በትምህርት ባለድርሻ አካላት እኩል ተሳትፎን የሚጠይቅ ነው ያሉት ዶክተር ቤታ፤ በመሆኑም የትምህርት ዘርፉን በበላይነት የሚመሩ አካላት ትርጉም ያለው ተሳትፎ እና ሁሉን አቀፍ መድረኮችና ዘዴዎች ሊጠቀሙ እንደሚገባ አሳስበዋል።

መምህራንን፣ የመንግሥት እና የግል ሴክተሮችን፣ ወላጆችን፣ ተማሪዎችን እና የዘርፉን ባለሙያዎች በንቃት ማሳተፍ የትምህርት ሥርዓቱ የተማሪዎችን ፍላጎት እንዲያሟላ፣ የበለጠ ምላሽ ሰጪ፣ አካታች እና የተሻለ እንዲሆን ያደርጋል ብለዋል።

የፖሊሲ ውሳኔዎችን በማሳወቅ ረገድ የመምህራን እውቀት እና ልምድ በዋጋ ሊተመን የማይችል ሲሆን፤ ከግሉ ሴክተር ጋር ያለው ትብብር ደግሞ አዳዲስ መፍትሔዎችን እና ግብዓቶችን ሊያመጣ እንደሚችል ተናግረዋል።

# ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ በ2016 ከ2 ሺህ በላይ የግብርና ማሽነሪዎችን ያመርታል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮ ኢንጅነሪንግ ግሩፕ በ2016 በጀት ዓመት ከ2 ሺህ በላይ የግብርና ማሽነሪዎችን ለማምረት ማቀዱን አስታውቋል፡፡

በኢትዮ ኢንጅነሪንግ ግሩፕ የፕላንና ፕሮግራም ኃላፊ አቶ መስፍን ተስፋዬ እንደገለጹት፤ በ2016ዓ.ም ሊኖሩ የሚችሉ ምቹ ሁኔታዎችን በመጠቀም ኢትዮጵያ የራሷ ብራንድ ይገባታል በሚል እሳቤ ግዙፍ ሀገራዊ ግቦችን ለመስራት ታቅዷል፡፡ በያዝነው በጀት ዓመት 2 ሺህ 782 የግብርና ማሽነሪዎችን ለማምረት እቅድ ተይዟል፡፡ እንዲሁም ከ2 ሺህ በላይ የዋየርና ኬብል ምርት በማምረትና ለተጠቃሚዎች ለማሰራጨት አቅዷል፡፡ በብረታብረት መለዋወጫ ዘርፍ ከ1 ሺህ 800 በላይ ቶን ምርት ለማምረት የታቀደ ሲሆን፤ ከባለፈው ተመሳሳይ ዓመት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ጭማሪ አለው፡፡

እንደ አቶ መስፍን ገለጻ፤ በኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ በተሠራ የማሻሻያ ሥራ ሀብትን ከምዝበራ ማስቆም፣ አዲት ወደሚደረግበት አቋም እንዲመጣ ማድረግና በ2015ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ትርፋማ እንዲሆን አስችሎታል፡፡

ባለፉት አምስት ዓመታት የሀገር ውስጥ ግብርና መካናይዜሽን እንዲደግፉ ከ9ሺህ በላይ ትራክተሮች፣ ፓምፖችና የተለያዩ ማሽነሪዎችን በማምረት ለተጠቃሚዎች አስራጭቷል፡፡ እንዲሁም ከቀላል እስከ ከባድ ከ1 ሺህ በላይ ተሽከርካሪዎችን አምርቶ ለሀገር ውስጥ ገበያ አቅርቧል፡፡ በከፍተኛ ሁኔታ የግብዓት አቅርቦት ሁኔታ በመኖሩ የሚመረቱ ምርቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሱ መምጣታቸውን ገልጸዋል፡፡

እንደ ተቋም በግብርና መካናይዜሽን የበኩሉን ሚና መወጣት አለበት በሚል ከፍተኛ ሥራ እየሠራ መሆኑን የገለጹት ኃላፊው፤ ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ የትራክተር ምርቶችን ወደ ማምረት መሸጋገር ያስፈልጋል፡፡ የመስኖ ውሃ ቆጣቢ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ማምጣትና የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በሀገር ውስጥ ማምረት በሚቻልበት ሁኔታ እቅዶች አሉ፡፡ በግንባታው ዘርፍ እገዛ ለማድረግ በትኩረት እየተሠራ ነው፡፡ ሰፋ ያለ እቅድ በማስቀመጥ የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎና አቅም በማስተባበር ያስቀመጥነውን ግብ ለማሳካት ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡

በዘርፉ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት ከባለድርሻ አካላት ጋራ መሥራት ይገባል፤ በተለይ ከውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ጋር ያሉ ችግሮች መቀረፍ አለባቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ለተቋሙ ምርታማነት ፈተና ደቅኗል፡፡ በርካታ ያልተሰበሰበ ተሰብሳቢ ሂሳብን በመሰብሰብ አቅምን ማሳደግ ይገባል፡፡ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የገበያ ትስስር ላይ በጋራ መሥራት አስፈላጊ ነው ሲሉም አቶ መስፍን ገልጸዋል፡፡

# በ2016፤ ከ16 ሺህ ኪሎ ሜትር በላይ የመንገድ ግንባታና ጥገና ይከናወናል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ከ16 ሺህ ኪሎ ሜትር በላይ የመንገድ ግንባታ እና ጥገና ሥራዎችን ለማከናወን መታቀዱን የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር አስታወቀ፡፡ ባለፈው በጀት ዓመት 13 ሺህ ኪሎ ሜትር በላይ የመንገድ ግንባታ እና ጥገና ሥራዎች መሥራቱን አመልክቷል፡፡

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የሕዝብ ግንኙነት ቡድን መሪ አቶ አብርሀም አማረ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አስተዳደሩ በተያዘው በጀት ዓመት ከ16 ሺህ 944 ኪሎ ሜትር የመንገድ ግንባታ እና ጥገና ሥራዎችን ለማከናወን ታቅዶ እየተሠራ ነው፡፡ እነዚህ የመንገድ ጥገናና ግንባታዎችም 76 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር ወጪ የሚሠሩ ይሆናል፡፡

በጀት ዓመቱ ከ16 ሺህ 944 ኪሎ ሜትር የመንገድ ግንባታ እና ጥገና ሥራዎች ውስጥ 15 ሺህ 700 ኪሎ ሜትር የሚሆነው ጥገና የሚያስፈልጋቸውን መንገዶች ለመጠገን መታቀዱን ገልጸዋል፡፡

ቀሪው አንድ ሺህ 244 ኪሎ ሜትር የሚሆነው የአዲስ ግንባታ ሥራዎች ፣ የመንገድ ፕሮጀክቶችን የማጠናከር እና የማሻሻል ሥራ ይሠራል ብለዋል፡፡

ለመንገድ ጥገናና ግንባታ ሥራዎቹ ተገቢውን ክትትል በማድረግ በበጀት ዓመቱ የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ እንደሚሠራም አመልክተዋል።

አስተዳደሩ በመካሄድ ላይ ያሉ ነባር ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት በማድረግ ፕሮጀክቶች በኮንትራት ውላቸው መሠረት እንዲጠናቀቁ በቅርበት



አቶ አብርሀም አማረ

እንደሚከታተል ጠቁመው፤ለዚህም የፕሮጀክቶች አስተዳደር ጽህፈት ቤቶች በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች እንዲደራጁ መደረጉን አስታውቀዋል፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የኮንስትራክሽን ዘርፉ እና በተለይም የመንገድ ግንባታው በተለያዩ ውስብስብ እና ጥልቅ ችግሮች እየተፈተነ ነው ያሉት አቶ አብርሀም፤ ይህንንም ለመፍታት የመንገድ ግንባታ ዘርፍ አቅሙን እያጎለበተ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን ለመሻገር እና የሀገሪቱን ሁለንተናዊ ልማት ለመደገፍ ጥረት እያደረገ ይገኛል ብለዋል።

በግንባታ ሂደት ላይ ያሉ እና ግንባታቸው ለዘገየ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ማሻሻያ ስትራቴጂ ቀርፆ ተግባራዊ እንደሚደረግ ጠቁመው፤ የተጎዱ መንገዶችን እና ድልድዮችን በአፋጣኝ ጥገና በማከናወን የትራንስፖርት እንቅስቃሴው እንዲቀላጠፍ ማድረግ የእቅዱ አካል መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ጊዜያዊ ድልድይ በተሰራባቸው አካባቢዎች የቋሚ ድልድይ ሥራን የማስጀመር ተግባር የሚከናወን መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም ከተጀመሩ ረጅም ጊዜ ለሆናቸው ፕሮጀክቶች ግልጽ የማጠናቀቂያ ስትራቴጂና እቅድ አውጥቶ የማጠናቀቅ ሥራ የሚሠራ መሆኑን ነው አቶ አብርሀም የተናገሩት፡፡

የተቋረጡ ፕሮጀክቶችን ደረጃ በደረጃ ማስጀመር እና እስኪጀመሩ ድረስ የትራንስፖርት አገልግሎት መስተጓጎል እንዳያጋጥም ከመንገድ ሀብት ማኔጅመንት ጋር እንደሚሠራም አስታውቀዋል፡፡

በተጠናቀቀው 2015 የበጀት ዓመት 13 ሺህ 845 ኪሎ ሜትር የመንገድ ግንባታ እና ጥገና ሥራዎች መሥራቱን አስታውሰው፤ 953 ኪሎ ሜትር አዳዲስ መንገዶች ግንባታ እና 12 ሺህ 892 ኪሎ ሜትር የመንገዶች ጥገና ተከናውኗል ብለዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር በተለያዩ ችግሮች ምክንያት በአንዳንድ አካባቢዎች ፈርሰው ለነበሩ 11 ድልድዮች ከ232 ሚሊዮን ብር በሚበልጥ ወጪ የመልሶ ግንባታ ሥራ ተከናውኗል፡፡ 2015 በጀት ዓመት ከተበጀተው 65 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር የካፒታል በጀት ውስጥ የችሮታ ጊዜን ጨምሮ 51 ቢሊዮን ብር ወጪ መደረጉንም አቶ አብርሀም አስታውቀዋል፡፡

# ብሔራዊ መግባባት ለመፍጠር ሀገራዊ እሴቶቻችንን እንዴት እንጠቀምባቸው?

ፋንታነሽ ክንዴ

ኢትዮጵያውያን ለዘመናት ተከባብረውና ተቻችለው ሀዘናቸውን ሆነ ደስታቸውን እየተጋሩ በጋራ ኖረዋል:: በዘመናት ሂደት በተፈጠሩ የባእዳን ትርክቶች ምክንያት አለመግባባቶች ሲፈጠሩ ይስተዋላል:: እነዚህ ልዩነቶች እየሰፉ ሄደው ዛሬ ላይ እዚህም እዚያ ግጭቶች ሲፈጠሩ ይስተዋላል:: ይህን ችግር ለመቅረፍም ሀገራዊ ምክክር ለማካሄድ የምክክር ኮሚሽን ተቋቁሞ የዝግጅት ሥራዎችን በማጠናቀቅ ላይ ይገኛል::

የዘርፉ ምሁራን ኢትዮጵያውያን አብሮነትን የሚያጠናክሩ፣ ችግሮች ሲፈጠሩም የሚፈቱበት ቱባ ሀገር በቀል እውቀቶች አሉና በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ መዋል እንዳለባቸው እያሳሰቡ ነው::

በጉዳዩ ላይ አስተያየታቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሰጡት በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል አንትሮፖሎጂ መምህር አቶ አንዷለም አሰፋ እንደሚሉት፤ የሀገራዊ ምክክር ዋና ዓላማዎች ግንዛቤ መፍጠር፣ የጋራ መግባባት መገንባት እና ለአሳሳቢ ሀገራዊ ጉዳዮች መፍትሔ መፈለግን የሚያጠቃልሉ ናቸው:: በውይይቱ የተለያዩ አመለካከቶች እንዲሰሙና ትኩረት እንዲያገኙ በማድረግ አካታችነትን፣ ተጠያቂነት እና ዲሞክራሲ የሚጎለብትበት ዘዴ ተደርጎ ይወሰዳል። በተጨማሪም እርቅ ለማውረድ፣ ግጭቶችን ለመከላከል፣ ለመፍታት ብሎም አወንታዊ ማኅበረሰባዊ ለውጦችን ለማምጣት ከፍተኛ ሚና አለው ይላሉ::

የውይይቱ ስኬታማነት የሚወሰነውም ተሳታፊዎች ትርጉም ያለው ውይይት ለማድረግ ባላቸው ዝግጁነት፣ በሂደቱ ላይ በሚኖሩ መግባባቶችና ስምምነቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ባለው ቁርጠኝነት ነው የሚል ሃሳብ አላቸው።

በውይይት ሂደቱ ውስጥ ባህላዊ እሴቶችን ማካተት እና መጠቀም የውይይቱን ውጤታማነትን ከፍ እንደሚያደርግ የሚያመላክቱት ምሁሩ፤ እነዚህ ባህላዊ እሴቶች በነጻነት የሚንሸራሸሩበትን መድረክ መፍጠር ተሳታፊዎች አመለካከታቸውን እና ፍላጎቶቻቸውን በነጻነት እንዲገልጹ በማድረግ አካታችነትንም የሚያሳድግ



ዶክተር ሮባ ጴጥሮስ

መሆኑን ይጠቅሳሉ::

ነባር እሴቶቻችን ብዙውን ጊዜ አካታች ተሳትፎን የሚተገብሩ እና የጋራ ውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓትን የሚያበረታቱ ናቸው:: በመሆኑም ሀገራዊ ምክክሩ ላይም ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎችና ባህላዊ እሴቶቻቸውን ከማሳተፍ ባሻገር ሀገር በቀል ባህላዊ የውይይት እና የግጭት አፈታት ሂደቶችን እና ልምዶችንም የሀገራዊ ምክክሩ አካል ማድረግ የተሻለ ውጤትና የጋራ መግባባት ላይ ለመድረስ ትልቅ ሚና ይኖረዋል የሚል እምነት እንዳላቸው ያስረዳሉ::

የውይይቱ አውድ እና ሂደት የኅብረተሰቡን ነባር ባህላዊ እሴቶች ያገናዘበና የሚያንጸባርቅ በማድረግ ባህላዊ እሴቶቻችንን በመጪው ሀገራዊ ምክክር ላይ መጠቀም ይቻላል ነው ያሉት::

እንደ ምሁሩ ገለጻ፤ በደቡብ አፍሪካ፣ በኬንያ፣ በቱኒዚያ፣ በኮሎምቢያ፣ በማይናማር የተለያዩ ሀገራዊ ችግሮችና አለመግባባቶችን ለመፍታት በተካሄዱ ብሄራዊ ውይይቶች ላይ ሀገራዊ አስተሳሰቦች፣ ፍልስፍናዎች፣ የግጭት አፈታት ሂደቶችና ሀገር በቀል እውቀቶች ጥቅም ላይ ውለዋል::

ሀገራዊ እሴቶቻችን ይቅር ባይነትን፣ የጋራ መግባባትን፣ ማኅበራዊ ትስስርን፣ ደስታንም ሆነ ችግርን አብሮ መወጣትን የሚያበረታቱና የሚከውኑ መሆናቸውን ያመላከቱት አቶ አንዷለም፤ በሀገራዊ ምክክሩ ላይም ለእነዚህ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲሸጋገሩ ለቆዩ የይቅር ባይነት እና መተባበር ባህላዊ እሴቶች ትኩረት ቢሰጥ የተሻለ ውጤት ማምጣት ያስችላል ይላሉ::

በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት ኃላፊ ሮባ ጴጥሮስ(ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያውያን ለዘመናት የገነቡት ተግባብቶ፣ ተቻችሎና ተከባብሮ በጋራ የመኖር ትልቅ እሴት አላቸው:: እነዚህ እሴቶች በጽሑፍ ባይቀመጡና በፖሊሲ ማእቀፎች ውስጥ ተገቢው ጥበቃና ከለላ ባይደረግላቸውም ማኅበረሰቡ በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ይጠቀምባቸዋል ይላሉ::

ግጭት ሲፈጠርም እነዚህን ነባር እውቀቶች ተጠቅሞ ሰላማዊ ኑሯቸውን የሚረብሽ ሁኔታ እንዳይፈጠር ይሠራሉ የሚሉት ዶክተር ሮባ፤ እንደ ሀገር በሚካሄደው ሀገራዊ ምክክር መድረኮችም በየአካባቢው ያሉ ነባር እሴቶቻችን በአግባቡ ትቅም ላይ ማዋል ይጠበቅብናል ባይ ናቸው::

ሩዋንዳን ጨምሮ ሌሎችም በርካታ ሀገራት ውስጣዊ ችግራቸውን ለመፍታት ሀገር በቀል እውቀቶችን መጠቀማቸውን አስታውሰው፤ በኢትዮጵያ በአራቱም አቅጣጫ ስንሄድ ማኅበረሰቡ ለችግር መፍቻነት የሚጠቀምባቸውን እሴቶች የጋራ ማድረግና ችግሮቻችንን ለመፍቻ ቁልፍነት መጠቀም ያስፈልጋል ነው ያሉት::

ለዚህ ሂደት መሳካት ደግሞ መንግሥት፣ ምሁራንና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት በቁርጠኝነት መሥራት እንዳለባቸው ያስገነዝባሉ::

እንደ ባለሙያዎቹ ገለጻ፤ በርካታ ሀገራት ያጋጠማቸውን ችግር በመፍታት ሂደት ሀገር በቀል እውቀቶችን በስፋት ተጠቅመዋል:: ኢትዮጵያውያንም ያለንን ሀገር በቀል እውቀት ለሀገራዊ ምክክሩ በአግባቡ ብንጠቀም ለምክክሩ መሳካት ትልቅ ግብዓት ሆኖ ያገለግላል::

በመሆኑም መንግሥት፣ የምክክር ኮሚሽኑ፣ ምሁራንና ሌሎችም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን እነዚህ ሀገር በቀል እውቀቶች በተገቢው መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ኃላፊነታቸውን መወጣት እንዳለባቸው አመልክተዋል::

## የኢሬቻ በዓል...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከዶዶላ ከተማ የመጡት ወይዘሮ ጌጤ ቱራቃበቶ ለኢፕድ እንደገለጹት፤የኦሮሞ ሕዝብ መገለጫ የሆነው ኢሬቻ ፍቅርና አንድነት የሚሰበክበት ነው።

ኢሬቻ የኦሮሞ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን የብሔር ብሔረሰቦች በዓል ነው ያሉት ወይዘሮ ጌጤ የኦሮሞ ሕዝብ በአቃፊነት በዓሉን ያከብራል ብለዋል።

የአሁኑ ትውልድ ማንነቱን፣ ባህሉንና አንድነቱን ሊጠብቅ እንደሚገባ ጠቅሰው፤ ያለችን ሀገር አንድ በመሆኗ ተቻችሎና ተከባብሮ መኖር የግድ መሆኑንም ገልጸዋል።

ከቡራዩ ከተማ የመጣው ወጣት ድርቤ ደበሌ በበኩሉ፣ የዘንድሮው የኢሬቻ በዓል የኦሮሞን ሕዝብ ጨምሮ ብሔር ብሔረሰቦች የታደሙበት በመሆኑ ኢትዮጵያዊ አንድነትና ወንድማማችነት በጉልህ የታየበት ነው።

የኢሬቻ በዓል ከንጋት ጀምሮ የኦሮሞን ሕዝብ ባህላዊ እሴት ጠብቆ መከበሩን የገለጸው ወጣት ድርቤ፤ አንድነትና ወንድማማችነትን በኢሬቻ አይተናል ብሏል።

የኦሮሞ ሕዝብ አቃፊ በመሆኑ የተለያዩ ብሔረሰቦች በኢሬቻ በዓል ተሳትፈዋል ያለው ወጣቱ፤ በኢሬቻ የታየው ወንድማማችነት ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ ገልጿዋል ።

ከባሌ ከተማ የመጣችው ወጣት ሀያት አረባ በበኩሏ፤ የኢሬቻ በዓል ሰላማዊና ባህላዊ እሴቱን በጠበቀና አንድነትና ወንድማማችነትን ማዕከል ባደረገ መልኩ እየተከበረ ነው ብላለች።

ኢሬቻ ሰላም ፍቅርና አንድነት የሚሰበክበት በዓል ነው ያለችው ወጣት ሀያት፤ ወጣቱ በዓሉን ሲያከብርም ሆነ ከበዓሉ በኋላ ሰላሙን ማስጠበቅ እንዳለበት ገልጻለች።

ወጣቱ የሰላሙ ባለቤት በመሆኑ ሰላምን መስበክና አንድነቱን መጠበቅ እንዳለበትም በአጽንኦት ገልጻለች።

ከጋሞ ዞን የኢሬቻ በዓል ለመታደም የመጡት አቶ አመለ አልቶ በበኩላቸው፤የዘንድሮው የኢሬቻ በዓል ከአምና የተሻለና የኢትዮጵያውያን አንድነት ይበልጥ ጎልቶ የታየበት ነው ብለዋል።

ኢሬቻ የኢትዮጵያውን መገለጫ ባህል ነው ያሉት አቶ አመለ፤ የጋሞ ማኅበረሰብ በዓሉን ከኦሮሞና ከሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች ጋር በጋራ በማክበራቸው የተሰማቸውን ደስታ ገልጸዋል::

ኢሬቻ የሕዝብ ለሕዝብ ትስስር የሚጠናከርበት መሆኑን ጠቅሰው፤ አንድነትንና ወንድማማችነትን በሚገልጽ መልኩ ተከብሯል ብለዋል።

የዘንድሮው የኢሬቻ በዓል ከትናንት በስቲያ በአዲስ አበባ ሆረ ፊንፊኔ፣ ትናንት ደግሞ በቢሾፍቱ ሆረ ሀርሰዴ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም የውጭ ሀገር ቱሪስቶች በተገኙበት ተከብሮ ውሏል::

## ኢሬቻ እሴቱን ጠብቆ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጥላቻ ሲነዙ የነበሩ አካላት የኦሮሞ አንድነትና የሕዝቦች ወንድማማችነት ጠንካራ መሠረት ላይ ለመገንባቱ የበዓሉ በሰላምና በወንድማማችነት ተከብሮ መጠናቀቅ ማሳያ ነው ብለዋል::

በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ከአምስት እስከ ሰባት ሚሊዮን የሚገመት ሕዝብ የተሳተፈበት ታላቅ በዓል ያለምንም የፀጥታ ችግር መከበሩ ለሀገሪቱ ትልቅ ትርጉም ይኖረዋል ያሉት ኃላፊው፤ በአንድ በኩል የበዓሉ ባለቤት የኦሮሞ ሕዝብ ሰላም ወዳድ ታላቅ ሕዝብ መሆኑ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሀገሪቱ ሕዝብ ወንድማማችነት ከብረት የጠነከረ መሆኑን ዓለም ያየበት አጋጣሚ ነው ብለዋል።

በኢኮኖሚ አንጻርም የተለያዩ የፋሽን ዲዛይን የፈጠራ ውጤቶች የተስተዋሉበት በዓል ከመሆኑም በላይ በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ታዳሚዎችን በማሳተፉ ከፍተኛ የቱሪዝም መነቃቃት መፍጠሩን አመላክተዋል።

የኢሬቻ በዓል ፍጹም ሰላማዊ በሆነ መልኩ እንዲከበር የአዲስ አበባ ሕዝብና የቢሾፍቱ ከተማ ነዋሪዎች የበዓሉን ታዳሚዎች በኢትዮጵያዊ ጨዋነት በማስተናገዳቸው የክልሉ መንግሥት ከልብ የመነጨ ምስጋና ማቅረቡን አቶ ኃይሉ ገልጸዋል።

አባ ገዳዎች፣ ሀደ ሲንቄዎች፣ የክልሉ ወጣቶች፣ የሸገር ከተማ ነዋሪዎች በተለየ መልኩ ደግሞ በየደረጃው ያሉ የፀጥታ አካላት በፀጥታ ዙሪያ ያለምንም መታከት በሠሩት ሥራ የክልሉ መንግሥት ምስጋና አቅርቧል።

የኢሬቻ በዓል ከኢትዮጵያ አልፎ በጎረቤትና በውጭ ሀገሮች መከበር ከጀመረ ሰንበቷል ያሉት አቶ ኃይሉ፤ ኢትዮጵያ ከዓለም ጋር ያላትን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት በይበልጥ ለማጎልበት ኢሬቻን እንደ አንድ የዲፕሎማሲ መሳሪያ መጠቀም እንደሚጠቅማት አስገንዝበዋል።

የክልሉ መንግሥትም በተለያዩ ሀገራት የሚከበረው የኢሬቻ ክብረ በዓል ተጠናክሮ እንዲቀጥል በቁርጠኝነት እንዲሚሠራ አቶ ኃይሉ ተናግረዋል።

## ኮሚሽኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በዚህም መንግሥት በሀገራዊ ምክክሩ የሚጠበቅበትን እንዲወጣ ስለሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ግንዛቤ እንዲኖረው ተደርጓል ያሉት ቃል አቀባዩ፤ ኮሚሽኑ የምክክር ሂደቱን ከሚመራበት መሰረታዊ መርሆዎች አኳያ ከባለድርሻ አካላት ጋር ያከናወናቸው ውይይቶች ስኬታማ መሆናቸውን ገልጸዋል።

"ኮሚሽኑ በተቋቋመበት አዋጅ መሰረት ገለልተኛ ነው። ተጠሪነቱም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው" ያሉት ቃል አቀባዩ፤ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ በርካታ ባለድርሻ አካላት አሉት። ከነዚህ ባለድርሻ አካላት አንዱ መንግሥት መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ ቃል አቀባዩ ገለጻ፤ የኮሚሽኑ ሥራ የሚከናወነው በአራት ምዕራፎች ተከፍሎ ነው። አንደኛው የቅድመ ዝግጅት ሥራ የሚከናወንበት ምዕራፍ ሲሆን፤ ሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ የዝግጅት ምዕራፍ ነው። ሦስተኛ የሂደት ምዕራፍ ነው። አራተኛው ምዕራፍ የመጨረሻው ምክክር ሲሆን፤ በዚህም ለሀገራዊ ችግሮች መፍትሔ የሚገኝበት ነው።

በቅድመ ዝግጅት ምዕራፍ ሀገራዊ ምክክር በዓለም ደረጃ አዲስ ባይሆንም በሀገራችን የመጀመሪያው መሆኑን እና ሀገራዊ ምክክር በተደረገባቸው ሀገራት ዙሪያ ያሉ መረጃዎችን የመዳሰስና የመገንዘብ ሥራዎች ተከናውነዋል። በሂደቱም የኮሚሽኑ ኮሚሽነሮች ከተለያዩ አካባቢዎች የተውጣጡ በመሆናቸው እርስ በእርስ እንዲግባቡና እንዲናበቡ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል ብለዋል።

የሦስት ዓመት እቅድና ዓመታዊ እቅድ የማዘጋጀት፣ የኮሚሽኑንን የመፈጸም አቅም የማሳደግ እና ተሳታፊዎችን መለየት የሚያስችል የአሰራር ሥነ ዘዴ የማዘጋጀት ሥራ በኮሚሽኑ የሁለተኛ ምዕራፍ ሥራ ማለትም በዝግጅት ምዕራፍ የተከናወኑ ሥራዎች መሆናቸውን ተናግረዋል።

ኮሚሽኑ የሂደት ምዕራፍ ላይ ይገኛል። በዚህም በአምስት ክልሎችና በሁለት የከተማ አስተዳደሮች የተሳታፊ ልየታ የተከናወነ ሲሆን፤ የተሳታፊ ልየታ ባልተደረገባቸው አካባቢዎች በቅርቡ የተሳታፊ ልየታ እንደሚደረግ ገልጸዋል።

የኮሚሽኑ የሥራ ሂደት ውጤታማ እንዲሆን የሌሎች ሀገራት የምክክር ሂደትን የማጥናትና ተሞክሮ የመቅሰም ሥራ እንደተከናወነ የገለጹት ቃል አቀባዩ፤ ምክክር በራሱ ሳይንስ በመሆኑ ኮሚሽኑ ሳይንሳዊ ሂደቶችን ይከተላል። ተሳታፊ የሚለይበት መንገድ እና አጀንዳ የሚመረጥበት ሂደት በሳይንሳዊ መንገድ የተከናወነ ነው። በዚህም ሀገር በቀል እውቀቶችን የመጠቀም ሥራ ተሠርቷል ብለዋል።

በሀገሪቱ ችግሮችን በውይይት የመፍታት ልምድ ዝቅተኛ መሆኑ በኮሚሽኑ ሥራ ላይ ተግዳሮት ሆኗል። ችግሩንም ለመፍታት ለተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራዎች ተከናውነዋል። ቃል አቀባዩ ተግዳሮቶቹ ኮሚሽኑ ከያዘው ዓላማ አንፃር አነስተኛ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል እና በአንዳንድ ቦታዎች የነበሩ ግጭቶች ሥራዎች በተቀመጠላቸው ጊዜያት እንዳይከናወኑ እንቅፋት ቢሆኑም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በተደረገ ውይይት ችግሮቹን ለመፍታት እንደተሞከረም ተናግረዋል።

ኮሚሽኑ የሠራቸውን ሥራዎች ውጤታማነት የሚገመግመው ኮሚሽኑ ካዘጋጀው እቅድ አኳያ እና በአዋጅ ከተሰጠው ኃላፊነት አንፃር መሆኑንም ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሰብዓዊነት ይቅደም!

በሀገሪቱ የለውጥ መንፈስ በዜጎች ሕይወት ውስጥ አቅም ገዝቶ መንቀሳቀስ ከጀመረበት ጊዜያት አንስቶ የለውጥ ባህሪ ነውና ሀገር እንደ ሀገር ብዙ ዋጋ ለመክፈል ተገዳለች። ለቀደመው የፖለቲካ ሥርዓት አልገዛም ከማለት ጀምሮ ፣ መላው ሕዝባችን የለውጡ ተስፈኛ በመሆን ከፍ ያለ መስዋዕትነት የጠየቁ ታሪካዊ ክስተቶችን ለማስተናገድ የተገደደባቸው ሁኔታዎች ብዙ ናቸው።

እንደሀገር ቀደም ባሉት ጊዜያት ከነበሩን የለውጥ ተሞክሮዎቻችን በመነሳት ፣ ለውጡን ያልተገባ ዋጋ መክፈያ ሳይሆን የተሻለ ማትረፊያ ለማድረግ በለውጥ ኃይሉ በኩል የተደረጉ ጥረቶች ፣ ይዘናቸው ከመጣናቸው የኃይል እና የሴራ ፖለቲካ ምክንያት ብዙ ፈተናዎችን አስተናግዷል።

በአንድ በኩል የለውጡ መንፈስ ያልጣማቸው ፣ ራሳቸውን አልፋና ኦሜጋ አድርገው የሚቆጥሩ ኃይሎች፤ በሌላ በኩል በየዘመኑ ሀገራዊ ክፍተቶችን አነፍንፈው የክፍተቱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚጥሩ ታሪካዊ ጠላቶቻችን በጋራ ሆነው በፈጠሩብን ሀገራዊ የህልውና ስጋት ሳንወድ በግድ ወዳልተፈለገ የግጭትና የጦርነት አዙሪት ተመልሰን ልንገባ ተገደናል።

በዚህም በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎቻችን ለሞት እና ለአካል ጉድለት ፣በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ለስደትና ለመፈናቀል፣ ለረሀብና ለእርዛት ፣ ሌሎች በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ደግሞ ለስነልቦና ቀውስ የተዳረጉበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ችግሩም ሆነ ከችግሩ በስተጀርባ ያሉ ገኸ ምክንያቶች ምንነት ለመላው ዓለም ያልተሰወረ፤ የአደባባይ ምስጢር ነው።

ይህ በሆነበት ሁኔታ አንዳንድ የዓለም አቀፍ ኅብረተሰብ ክፍሎች፤ የተሻሉ ነገዎችን አምጦ ለማዋለድ ባደረገው ጥረት ባልተገቡ ምክንያቶች ያልተገቡ ዋጋዎችን ለመክፈል ለተገደደው ሕዝባችን ፈጥኖ ከመድረስ ይልቅ የተስፋ ቀናቶችን ባልተገቡ ምክንያቶች እያበከነበት ይገኛል። ይህ ድርጊቱም ከሁሉም ይልቅ ከሰብዓዊነት አንጻር ጥልቅ ጥያቄን ሊያስነሳ የሚችል ነው።

አሁን በችግር ውስጥ ያለው ሕዝባችን የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አንድ ነው፤ ከችግሩ መውጣት እንዲችል የሚያስችለውን የትኛውንም አይነት ድጋፍ የማግኘት የሞራል ብቻ ሳይሆን የሕግም መብት አለው። ይህንን መብቱን በማስከበር ሂደት ውስጥም የሀገራት መንግሥታት እና ዓለም አቀፍ ተቋማት ያላቸው ኃላፊነት መተኪያ የሌለው ነው።

በተለይም እንደ የዓለም የምግብ ድርጅትን የመሳሰሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት ራሳቸውን ከየትኛውም የፖለቲካ ተጽእኖ ነጻ በማድረግ የዕለት እርዳታ ለሚፈልጉ ዜጎቻችን ተገቢውን ድጋፍ የማድረግ ግዴታ አለባቸው። ይህንን ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው ለሚፈጠረው ሰብአዊ ቀውስ ተጠያቂ ሊያደርጉት የሚችል አካልም ሊኖር አይችልም

በእያንዳንዱ ችግር ዙሪያ ተጠያቂነትን ለመፍጠር የሚደረግ ጥረት የርዳታ ተቋማቱ ኃላፊነት ሳይሆን ለዚህ የተቋቋሙ ሌሎች ዓለም አቀፍ ተቋማት ኃላፊነት ነው። እንዲህ ዓይነቱን የማጣራት ሂደት የችግሩ ባለቤት ያልሆነውን ሕዝብ በመቅጣት ውጤታማ ማድረግ አይቻልም። ውጤታማ አደርጋለሁ ብሎ መንቀሳቀስም ከተቋማዊ ስልጣንና ኃላፊነት በአደባባይ ማፈንገጥ ነው።

ይህን ዓለም አቀፋዊ እውነታ ተሳቢ በማድረግም ዓለም አቀፍ የምግብ ድርጅትን ጨምሮ፤ ራሳቸውን ዓለም አቀፍ የርዳታ ድርጅት አድርገው በመሰየም የሚንቀሳቀሱ ተቋማት ካለፈቃዱ በከፋ ችግር ውስጥ ለሚገኘው ሕዝብ በትንሹ የዕለት ደራሽ እርዳታዎችን በማቅረብ ከፊቱ ከሚጠብቀው አደጋ መታደግ ይጠበቅባቸዋል።

ይህን ላለማድረግ የሚቀርብ የትኛውም ዓይነት ምክንያት በተቋማቱ ላይ የሰብአዊነት ተጠያቂነት የሚያመጣና የሞራልም ሆነ የሕግ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ይሆናል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ:- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ከስኬቶቻችን የበለጠ ተጠቃሚ ለመሆን ለሰላማችን ዘብ ልንቆም ይገባል

**ይቤ ከደጃች.ውቤ**

አዲስ ዓመት ሰዎች ተስፋ የሚያደርጉበት፣ በጎ ነገር ለማድረግ የሚነሳሱበት፣ የተለያዩ እቅዶችን ለመፈጸም ሰፋ ያለ እንቅስቃሴ የሚያደርጉበት ጊዜ ነው ማለት ይቻላል:: በተለይ ደግሞ ኢትዮጵያውያን ከክረምቱ የጨለማ ወቅት ወጥተው ወደ አዲሱ ዘመን እና ወደ ብርሃን የሚሸጋገሩበት ስለሆነም በደስታ ይቀበሉታል::

የዘመን መለወጫን ፣ መስቀል ፣ የነብዩ መሐመድ ልደት (መውሊድ)በዓላትን በተከታታይ አክብረን የኢሬቻ በዓልን ለማክበር ደግሞ በዝግጅት ላይ እንገኛለን:: እነዚህን በዓላት ተከትሎ ደግሞ ከመስከረም 17 ጀምሮ ደግሞ ዓለም አቀፍ የቱሪዝም ቀን ይከበራል:: የዓለም ቱሪዝም ቀን ሲከበር የተለያዩ መርሀ ግብሮች ይኖሩታል:: ታሪካዊና ሰው ሰራሽ ቅርሶችን የመጎብኘት፣ቀኑን አስመልክቶ ፓናል(ውይይቶች) ማካሄድ፣ ጥቂቶቹ ናቸው::

የጀመርነው 2016 ዓመተ ምህረት በጎ ነገሮችን ከመባቻው እንካችሁ እያለን ይመስላል:: በጎ ነገሮቹ ሐሴት የሚያጭሩ ብቻ ሳይሆን፣ ዕሴት የሚጨምሩም ናቸው:: አንደኛው የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ 4ተኛ ዙር የውሃ ሙሌት መጠናቀቅ ያበሰረው ዜና ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ የግድብ ግንባታውን መጀመር በደስታ እንደተቀበለው ሁሉ፤የግድቡ አራተኛ ዙር የውሃ ሙሌት የመጠናቀቁን ብሥራት ሲሰማ ደግሞ የደስታ ስሜቱ ከፍ እንደሚል መገመት አያዳግትም::

> **የጀመርነው 2016 ዓመተ ምህረት በጎ ነገሮችን ከመባቻው እንካችሁ እያለን ይመስላል:: በጎ ነገሮቹ ሐሴት የሚያጭሩ ብቻ ሳይሆን፣ ዕሴት የሚጨምሩም ናቸው**

የ4ኛውን ዙር የውሃ ሙሌት መጠናቀቅ ተከትሎ የግድቡ ተጨማሪ /አምስት/ ተርባይኖች ወደ ሥራ ይገባሉ መባሉም ደስታውን እጥፍ ድርብ ያደርገዋል።ለብዙ ኢትዮጵያውያን ትልቅ ተስፋን የሰነቀው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ለጎረቤት ሀገሮችም በኤሌክትሪክ ኃይል ተደራሽ፣እንደሀገርም ከኤሌክትሪክ ሽያጭ የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ ጥቅሙን ዘርፈብዙ ያደርገዋል::

ጎረቤት ሀገሮች ከኢትዮጵያ በሚያገኙት ኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ከመሆን ባለፈ በሀገራቱ መካከል የሚኖረው የሁለትዮሽ ግንኙነቶች የጋራ ተጠቃሚነትን መሰረት ያደረጉ እንዲሆኑ የተሻለ እድል ይፈጥራል::

መስከረም 6 እና 7 ቀን 2016 ዓ.ም በሳዑዲ አረቢያ ሪያድ ከተማ በተካሄደው 45ኛው የዩኔስኮ የዓለም ቅርስ ጉባዔ ላይ የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክና የጌዴኦ መልክአ ምድርን በዓለም አቀፍ ቅርስነት በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ)መመዝገቡ ደግሞ ሌላው የአዲስ ዓመት የብሥራት ዜና ወይንም መልካም እሴት ነው::

የጌዴኦ ባሕላዊ መልክዓ ምድር በዩኔስኮ ዓለም አቀፍ ቅርስነት በተመዘገበበት በዚህ ዓመት የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክም በተመሳሳይ መመዝገቡ በደስታ ላይ ደስታን ፈጥሯል:: ከቱሪዝም ኮሚሽን ማኅበራዊ ሚዲያ ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ የጌዴኦ መልክዐ ምድር በውስጡ በርካታ እሴቶችን አካትቷል:: የመሬት አያያዙ፣ ታሪካዊ ቅርሶች፣ ትክል ድንጋዮች፣ (በዞኑ የተለያዩ ሥፍራዎች ከ6ሺህ በላይ ትክል ድንጋዮች መኖራቸው) የዋሻ ላይ ጽሑፍ እና በባሕላዊ መንገድ ብቻ የሚተዳደሩ ደኖች ጥቂቶቹ ይጠቀሳሉ::

በ1962 ዓ.ም የተቋቋመው የባሌ ተራራዎች ብሔራዊ ፓርክ የቆዳ ሥፋቱ 2150 ካሬ ኪ.ሜትር፤ የመሬት ከፍታው ከባሕር ጠለል በላይ ከ1ሺህ500 እስከ 4ሺህ337 ሜትር ይደርሳል:: በፓርኩ የኢትዮጵያ ሁለተኛ ትልቁ ተራራ ቱሉ ዲምቱ አንዱ ነው:: ለፓርኩ መመስረት በቀዳሚነት ምክንያት ከሆኑት መካከል ብርቅዬ የእፅዋት እና የዱር እንስሳት ዝርያዎች መገኘታቸው ነው:: በብሔራዊ ፓርኩ ውስጥ በጥናት ከተለዩት 1ሺህ660 የእጽዋት ዝርያዎች (40 በመቶ የሚሆኑት የመድኃኒትነት ፋይዳ ያላቸው)፤ 177 ዝርያዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ ናቸው::

ከዱር እንስሳት ዝርያ አንጻርም በሁሉም ምድቦች ብርቅዬ ዝርያዎች የተመዘገቡበት ፓርክ ነው:: ለአብነትም በሀገሪቱ ውስጥ ከተመዘገቡት 57 የአጥቢ ዝርያዎች፤ 22 ብርቅዬ ዝርያዎች በባሌ ተራራዎች ፓርክ ውስጥ የተመዘገቡ ናቸው:: ቀይ ቀበሮ፣ የደጋ አጋዘን፣ የባሌ ጦጣ በዋቢነት እንደሚገኙበት ከቱሪዝም ሚኒስቴር የተገኘ መረጃ ያሳያል::

ብሔራዊ ፓርኩ ኢትዮጵያን የአፍሪካ የውሃ ማማ ያሰኙት ከፍታማ ቦታዎች መካከል ትልቁን ድርሻ የያዘ ነው:: ከ40 በላይ ለሚሆኑ ወንዞች መነሻ ሲሆን፤ ድንበር ተሻጋሪ የሆኑት እንደ ዋቢ ሸበሌ፣ ገናሌ፣ ዱመል፣ ወልመል፣ ያዶት ወንዞች ይገኙበታል:: ከብሔራዊ ፓርኩ የሚነሱ ወንዞች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ወደ 30 ሚሊዮን ለሚሆኑ የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ፣ ሱማሌ እና ሰሜን ኬንያ ሕዝቦች አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው::

በሳዑዲ አረቢያ በተካሄደው በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት ጉባኤ ሁለቱ የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክና የጌዴኦ ባህላዊ መልክዓ ምድር በዩኔስኮ ዓለም አቀፍ ቅርስነት መመዝገባቸው ለኢትዮጵያ የምስራች ነው::

የዘንድሮ የዓለም የቱሪዝም ቀን ‹‹ቱሪዝም ለአረንጓዴ ልማት- አረንጓዴ ልማት ለቱሪዝም›› በሚል መሪ ቃል በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ44ኛ በሀገራችን ደግሞ ለ36ኛ ጊዜ እየተከበረ ነው። ይህም ሀገራችን እመርታ ያሳየችበትን ከአረንጓዴ አሻራችን ጋር የሚስተካከል መሪ-ቃል መሆኑ ይበልጥ ድምቀት ይሰጠዋል። ኢትዮጵያን በቱሪዝምም ሆነ በአረንጓዴ ልማት ያላትን ተቀባይነት ይበልጥ የሚያጎላ ይሆናል::

በዘንድሮው ዓመት በዮኔስኮ ዓለም አቀፍ ቅርስነት የተመረጡት የጌዴኦ ባህላዊ መልክዓ ምድርም ሆነ የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ በደንና ተፈጥሮ ልማት በሕዝቡ በትውፊት ለረጅም ጊዜ ተጠብቀው መኖራቸውም ‹‹ቱሪዝም ለአረንጓዴ ልማት- አረንጓዴ ልማት ለቱሪዝም›› የሚለው የቱሪዝም መሪ -ቃሉ በራሱ የሚገልፀው ነገር እንዳለ ያሳያል::

እርግጥ ነው ቀደም ብሎ የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ቦታዎች የሚጎበኙ የውጭ ቱሪስቶች በተለይ የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክን ሲጎበኙ እንደ ነበር ይታወቃል:: በዩኔስኮ ዓለም አቀፍ የተፈጥሮ ቅርስነት መመዝገቡ ግን ቱሪስቶችን የበለጠ እንዲስብ፣ የበለጠ ገቢ እንዲያመነጭ በር የሚከፍት እንደሚሆን ይታመናል::

ከነዚህ የአዲስ ዓመት የሀገር ብስራቶች / ስኬቶቻችን/ በአግባቡ ተጠቃሚ ለመሆን ግን ከሁሉም በላይ ለሰላማችን ዘብ ልንቆም ይገባል:: ለዚህ ደግሞ የግጭት መንገዶችን በሚቻለው አመራጭ ሁሉ መዝጋት፤ ችግሮችን ለዘለቄታው በውይይት የመፍታት ባህል ማዳበር ይጠበቅብናል።

# ነፃ ሃሳብ

# ትልቅ መሆን እየተመኘን ለምን አቃተን?

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ተግባር የሌለው የትልቅነት ምኞት መቀመቅ ነው:: በትናንት የሚያስኖር፣ ከታሪክ ሠሪነት አጉድሎ ታሪክ አውሪ የሚያደርግ የዝቅታ ቦታ ነው:: «ትልቅ ነበርን ትልቅም እንሆናለን» እንላለን:: ይሄን መፈክር ያልሰቀለ ግድግዳ፣ ያልተናገረ የመንግሥት አካልና ቢሮ የለም:: ተግባራችን ሲፈተሽ ለዚህ እውነት የሚሆን ብዙ ይቀረናል::

እውነት ነው እንደ ሀገር ትልቅ ነበርን:: ከራሳችን አልፈን ለዓለም የተረፈ የትልቅነት ሚና ነበርን:: በፖለቲካው፣ በዲፕሎማሲ ግንኙነት፣ በሠላሙ፣ በአስታራቂነት፣ በአንድነት፣ በወንድማማችነት የገነንን ሕዝቦች ነበርን:: ሥልጣኔና ዘመናዊነት መገኛቸው ከእኛ ዘንድ እስኪመስል ድረስ ምንም ለሆነችው ዓለም ፋናወጊዎች ነበርን::

አሁን ዘመን ተቀይሮ ከትልቅነት ወርደን ትልቅነትን የምንሽት ሆነን ተገኝተናል:: ትልቅ ነበርን እያልን ድሮን በማስታወስ በማይሠሩና በማያስቡ ወዲያ ወዲህ ማንነቶች ከከፍታችን ዝቅ ብለናል:: ትልቅ ያደረገንን ኢትዮጵያዊ ማንነት በብሔርና በዘር ሸንሽነን፣ ከፊት ያቆመንን የአብሮነት ኃይል በእኔነት መንዝረን ማንም ገፍትሮ የሚጥለው አቅመ ቢስ ልናደርገው እየተጋን ነው::

እንዴት ነበር ትልቅ ሀገርና ሕዝብ የሆንነው ብለን ብንጠይቅ፣ እንዴት ነበር ከዓለም ቀድመን ፊተኛ የሆንነው ብለን ብንመረምር በአንድነትና በወንድማማችነት ከፍ ሲልም በአንድ ገናና ስም የሚጠራ ኢትዮጵያዊነትን እናገኛለን:: አሁን ግን ይህ ትልቁ ስማችን ከብሔር ማንነታችን ቀጥሎ የሚጠራ ሆኗል::

ከብሔር ለጥቃ የምትጠራ ሀገር ትልቅ የመሆን ህልም እንጂ አቅም አይኖራትም:: ትርፉ ድካም ብቻ ነው:: ትልቅ መሆን አቅቶን በትልቅነት ምኞት አምናን እያስታወስን የምንዳክረው ተግባር በሌለው ህልም ነው:: ህልማችን ኢትዮጵያዊነትን ለብሶ፣ እኛነትን ተንተርሶ ወደመሆን እስካልመጣ ድረስ ትልቅነትን አንደርስበትም::

ምኞታችን ከብሔር ፖለቲካ ጸድቶ፣ ከአክራሪነት ነጥቶ ሁሉን አቃፊ እስካልሆነ ድረስ ግድግዳዎቻችን ምኞታችንን ከመስቀል፣ ፖለቲከኞቻችን ትልቅ ነበርን ትልቅም እንሆናለን ከሚል ትርክት የሚታደገው አይኖርም:: ትልቋ ኢትዮጵያ ዳግም ትልቅ ሆና እንድትመጣ በምኞታችን ውስጥ ለትልቅነት የሚያበቃ ሃሳብና ድርጊት፣ እርቅና ምክክር፣ ሠላምና ተግባቦት ያስፈልገናል::

አሁን አሁን አንዳንድ ድርጊቶቻችን ልጓም ለቆ ቼቼ ዓይነት ነው:: ልጓም ለቆ ቼቼ እንደምን ይቻላል? እርካብ ስቶ ግልቢያ፣ ፍቅርን ንቆ ጸጋ እንዴት ይሆናል? ሳንግባባ ትልቅነትን የምንመኝ፤ ሳንታረቅና አንድ ሳንሆን ትልቅ ነበርን ትልቅም እንሆናለን የምንል፤ ከጦርነትና ከጥላቻ እሳቤ ሳንወጣ እድገትና ብልፅግናን የምንሽት ሆነናል:: ትልቅነት በዚህ ውስጥ የለም:: ስለትልቅነት የተጻፉ አያሌ መጽሐፍት ትልቅነትን በዚህ መንገድ አልፈቱትም::

ትክክል ነገር መገኛው ትክክል የሆነ ቦታ ነው:: ፖለቲካችንን ሳናጸዳ፣ ሃሳቦቻችንን ሳንገራ እንደአባቶቻችን ትልቅ መሆን አንችልም:: በወንድማማችነት ሳንተቃቀፍ፣ በምክክር ወደአንድነት ሳንመጣ ከምንመኘው እውነት መድረስ አንችልም:: ዘረኝነትና ብሔርተኝነትን ገድለን ሳንቀብር፣ በወንድም ሞት ደም የተቀቡ ጎራዴዎቻችንን ወደአፎታቸው ሳንመልስ፣ ለሠላምና ለእርቅ ሳናጎነብስ ከፍ ማለት የማይታሰብ ነው::

> **ለትልቅነት** የሚያበቃ በሌለበት ሁኔታ ትልቅ ነበርን ትልቅም እንሆናለን ብለን ብንናገር ትርጉም አይኖረውም:: አባቶቻችን ትልቅ የነበሩት ለትልቅነት የሚያበቃ ፍቅርና አንድነትን ይዘው ነው:: እንደእኛ በብሔር ተቧድነው ሳይሆን ኢትዮጵያ በሚል የጋራ ስም ተጠርተው ነው

እስካሁን ከስረናል:: እየሄድንበት ያለው ነባራዊ ሁኔታ ትልቅነትን የሚሰጥ ሳይሆን ትልቅ እንዳንሆን መንገድ የሚዘጋ ነው:: መረቦቻችን ዓሣ እንዲይዙ፣ ሃሳቦቻችን እውነት እንዲጸንሱ ወደ ልክ የሚወስድ ልክ የሆነውን ጎዳና መከተል ግዴታችን ነው:: ሃሳብ ብቻውን አቅም የለውም:: ምኞት ብቻውን ሀገር አይፈጥርም::

ሀገር የምትፈጠረው ሀገር ለመፍጠር ብቁ በሆኑ ሃሳቦች ነው:: ትልቅነት የሚመጣው ለትልቅነት በተዘጋጁ አእምሮና ልቦች ነው:: ከድጡ ወደማጡ በሆነ ፖለቲካ፣ ሴራና መገፋፋትን ባነገበ የሥልጣን ሽኩቻ ሀገር የለችም:: የአቅጣጫ ለውጥ ያስፈልገናል:: ምኞታችን ጥሩ ሆኖ ሳለ ተግባራችን ግን ለምኞታችን የሚመጥን አይደለም:: ምኞታችንን የሚወልድ በእውቀትና በማስተዋል ከምንም በላይ ደግሞ በአንድነት የጎለመሰ ማንነት ያስፈልገናል::

በተለጠጠ የብሔር እሳቤ ውስጥ ሀገር ተፈጥራ አታውቅም:: የተለጠጠ የብሔር እሳቤ ሀገር የሚያኮስስ፣ ትውልድ የሚኮሰኩስ ነቀርሳ ነው:: ነገን የሚያጨልም፣ ተስፋን የሚያጠይም የዝቅታ ቦታ ነው:: መዳን አቅቶን ለግማሽ ክፍለ ዘመን የታመምነው በዚህ ነቀርሳ ነው:: ከዚህ ደዌ የሚፈውሰን እና ወደትልቅነት የሚወስደን በኢትዮጵያዊነት ስንታከም ነው::

የትኛውም ዓለም የሠለጠነው ሠልጥኖም ፊተኝነትን የተቀዳቸው በብሔር እሳቤ ሳይሆን በምክንያታዊነት ነው:: ምክንያታዊነት ደግሞ እውቀትን ተንተርሶ በሃሳብ የበላይነት ነፍስ የዘራ የምክክርና የውይይት ልማድ ነው:: እንድንግባባበት እና እንድንታረቅበት ከፊታችን ሰፊና ሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍል የሚያሳትፍ የምክክር ጉባኤ አለ::

ይሄ ጉባኤ በምክንያታዊነት ወደትልቅነት ለመሄድ ጥሩ አጋጣሚያችን ነው:: ችግሮቻችንን ነቅሰን በመፍትሔ ሃሳብ አርቀንና ታርቀን ወደአንድነት፣ ወደኢትዮጵያዊነት የምንመለስበት የተሐድሶ መድረክ ነው:: ከልዩነት ወጥተን ስለሀገራችን አንድ ዓይነት ሃሳብ የምናስብበት የእርቅና የመተቃቀፍ ጉባኤ ነው::

በሁሉም ነገር ተፈጥሯዊ ብዝሃነታችን ጉዳት የለውም:: ሀገር በመፍጠር ረገድ የተሳካላቸው ሀገራት የተለያየ ባህልና ሥርዓት፣ ልማድና ወግ ያላቸው ማኅበረሰቦች ናቸው:: እኛ ደግሞ በዚህ ነገር የታደልን ነን:: የልዩነት ዋጋው ሲገባን ብቻ ነው የተሣለች ሀገር መፍጠር እና ለመጪዎቹ ትውልዶች ማስተላለፍ የምንችለው::

ሕንድ ብዙ ማንነት ያላት ሀገር ናት፣ ቻይና፣ ናይጄሪያ፣ ደቡብ አፍሪካ ሌሎችም በርካታ ሀገራት በብዙ ልዩነት ውስጥ ሀገር የገነቡ ናቸው:: በዚያው ልክ ልዩነታቸውን ለኃይልና ለብርታት ያልተጠቀሙ ሀገራት ዕጣ ፈንታቸው እንደ ሩዋንዳና ዩጎዝላቪያ የከፋ ዋጋ ለመክፈል ይገደዳሉ::

ብሔር ከሀገር መቅደም የለበትም:: ብሔር ከሀገር ከቀደመ ልዩነት ጸጋ መሆኑ ቀርቶ መርገምት ሊሆን የሚችልበትን አደጋ ያስከትላል:: ከሀገር የቀደሙ ማንነቶች፣ አስተሳሰቦች፣ እምነቶች፣ ሥርዓቶች የኋላ ኋላ ዳፋቸው ለሁሉም የሚተርፍ ነው::

እዚህ ላይ የታዋቂውን አትሌት የቀነኒሳ በቀለን የአንድ ወቅት ንግግር ለመጥቀስ እገደዳለሁ:: ቀነኒሳ ስለብሔር ተጠይቆ ሲመልስ ልክ በሆነና ሁሉንም ባስማማ ሽጋ አገላለጽ ነበር:: ለእኔ አለ..‹ለእኔ ብሔር ማለት እንደ ጫማ እና ካልሲ፣ እንደ ልብስ እና ኮፍያ ተጨማሪዎች እንጂ ዋናዎች አይደሉም:: ዋናው ሀገር ነው› ሲል ነበር የተናገረው::

እውነት ነው ዋናው ሀገር ነው:: የብሔር እሳቤዎች ከሀገር ቀጥለው የሚመጡ ናቸው:: ሀገር ከብሔር ካልቀደመች፣ ኢትዮጵያዊነት ከእኔነት ካላለፈ ምኞታችን ሁሉ ውሃ ይበላዋል:: ወይም ደግሞ አሁን ላይ ትልቅ ነበርን ትልቅም እንሆናለን እያልን እንደምንመኛው ዓይነት ከንቱ ምኞት የማይደረስ ጉዞ ነው::

በሀገራችን በፖለቲካ ልዩነት የምንሰቃይበት፣ ወደጦርነት የምንገባበት የመገዳደል ልማድ ትልቁና ዋናው ትልቅነታችንን የሰወረብን ድርጊት ነው:: የማይገድል ፖለቲካ፣ የማይዋሽ ፖለቲከኛ እስካልተፈጠረ ድረስ ትልቅ መሆን አንችልም:: በነፃ መድረክ ስለሆነው እና እየሆነ ስላለው ጠያቂና ሞጋች ትውልድ እስካልፈጠርን ድረስ መታደስ አንችልም::

አባቶቻችን ትልቅ የነበሩት እኛ የሌለን እነሱ ያላቸው ወይም ደግሞ እኛ ያልገባን እነሱ የገባቸው እውነት ስላላቸው ነው:: ወደቀደመው ትልቅነታችን ለመመለስ ያልገባንን የአባቶቻችንን እውነት ፈልጎ ማግኘት አለብን:: ወደትልቅነት የሚወስዱ መሰላሎች በፍቅር የሚረገጡ፣ በአብሮነት የሚጀመሩ ናቸው:: ሁሉም የከፍታ ጎዳናዎች በመያያዝና በመደጋገፍ ጀምረው የሚያበቁ ናቸው::

የሌለን ምንድነው? አባቶቻችን ገብቷቸው እኛ ያልገባን የትልቅነት እውነት ምንድነው? ይሄ ጥያቄ ተግባር ከራቀው የትልቅነት ምኞት የሚያወጣን ወደአባቶቻችን የትልቅነት እውነት የሚያስጠጋን ነው:: ይሄ እውነት ከራቀንና ካልደረስንበት የከፍታ ምኞት የሚሰቅለን ነው:: የብዙዎቻችን ምኞት አንድ ዓይነት ነው:: ማደግ እንፈልጋለን፣ ሞትና ጉስቁልና የሌለባት ኢትዮጵያ እንድትፈጠር እንሻለን:: በፖለቲካው በማኅበራዊ ሕይወታችን የጥንቱን አብሮነት መልሰን በአንድ ስም መጠራት እንፈልጋለን::

ለዚህ ምኞታችን እውን መሆን የበኩላችንን ስንወጣ ግን አንታይም:: ጋን በጠጠር እንደሚደገፍ የኢትዮጵያ ተስፋና ህልም በእኛ ትንሽ መዋጮ ወደእውነትነት እንደሚቀየር ገና አልገባንም:: ማንን ነው የምንጠብቀው? ማን መጥቶ ከዝቅታ እንዲያነሳን ነው የምንጠብቀው? ሜዳውም ፈረሱም እጃችን ነው:: በፍቅርና በአብሮነት ተነስቶ መጋለብ የእኛ ፈንታ ነው::

አክሱምና ላሊበላን ያነጹ እጆች፣ የአፍሪካ እናት፣ የዓለም ምልክት..የፍጥረት ሁሉ በኩር ዛሬ ትልቅነት ርቋት በምኞት ስትዳክር ማየት ያሳዝናል:: የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል እንደሚባለው በፉክክር ውስጥ ሀገራችንን እያጎሳቆልናት ነው:: የፉክክር ፖለቲካ ሀገር አይገነባም:: በዓለም ታሪክ የፈረሱ ሀገራት በፉክክር ፖለቲካ ውስጥ ያለፉ ናቸው:: የፉክክር ፖለቲካ የማንነት ፖለቲካ ነው:: ብሔርና ዘርን መሠረት አድርጎ የሚገነባ ነው::

ብሔርና ዘር የቀደመበት ፖለቲካ የጋራ እሴት፣ የጋራ እውነት ለመጸነስ አቅም አይኖረውም:: ያለፈን እያስታወሰ፣ መጪውን እያቀደ የአንድን ማንነት የበላይነት የሚያቀነቅን ነው:: ትልቅ ነበርን ትልቅም እንሆናለን ብለን ስንናገር ትልቅ የሚያደርገንን ፖለቲካና ማኅበራዊ አንድነት ይዘን ሊሆን ይገባል::

ለትልቅነት የሚያበቃ በሌለበት ሁኔታ ትልቅ ነበርን ትልቅም እንሆናለን ብለን ብንናገር ትርጉም አይኖረውም:: አባቶቻችን ትልቅ የነበሩት ለትልቅነት የሚያበቃ ፍቅርና አንድነትን ይዘው ነው:: እንደእኛ በብሔር ተቧድነው ሳይሆን ኢትዮጵያ በሚል የጋራ ስም ተጠርተው ነው::

እውነት መነሻው እውነት ብቻ ነው:: ትክክል የሆነ ነገር በትክክል የሚያበቃ ነው:: አሁን ባለው ፖለቲካ፣ አሁን ባለው ማኅበራዊ አረዳድ እንዳባቶቻችን ያለ ትልቅ ሀገር ለመገንባት ብቁዎች አይደለንም:: ከጦርነትና ከብሔር እሳቤ ነፃ መውጣት አለብን:: አፋችን ላይ ያለችውን፣ ሆና ማየት የምንሻትን፣ ድምጽ ማጉያ በያዝን ቁጥር የምንናገርላትን ኢትዮጵያ ለመፍጠር የአባቶቻችንን የአንድነት መንፈስ ያስፈልገናል::

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# ከግብርናው ዘርፍ የተሻለ ውጤት ለማግኘት የሚደረግ ጥረት- በደቡብ ምዕራብ ክልል

**ፍሬሕይወት አወቀ**



የበርካታ ተፈጥሯዊና ማኅበራዊ እሴቶች ባለቤት የሆነው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ለእርሻና ለእንስሳት እርባታ ምቹ ሥነምህዳር ያለበት ክልል ነው:: ለክልሉና ለሀገራዊው ምጣኔ ሀብት ስትራቴጂክ ፋይዳ ካላቸው የግብርና ምርቶች መካከል ቡና፣ ቅመማ ቅመም፣ የቅባት እህሎችና ማር በስፋት ይመረትበታል:: በዚህም ከሀገር ውስጥ ፍጆታ ባለፈ በውጭ ምንዛሪ ግኝት ላይም የበኩሉን አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል:: ክልሉ በተለያዩ የሰብል ዓይነቶች፣ የቅባት እህሎች፣ በሆርቲካልቸር እንዲሁም በሥራ ሥር ምርቶች ይታወቃል::

ክልሉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን ከሚያገኙ የሀገሪቱ ክልሎች መካከል አንዱ ሲሆን፤ ይህም ክልሉ ከዓመት ዓመት አረንጓዴ ሆኖ እንዲታይ ከማድረጉም ባለፈ ለግብርና ሥራ ያለው አበርክቶ የጎላ ነው::

የክልሉ ግብርና ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊና የእርሻ ዘርፍ ኃላፊ አቶ አሸናፊ ክንፉ እንደሚሉት፤ ክልሉ በግብርናው ዘርፍ በ2015/16 ዓ.ም የመኸር ወቅት አጠቃላይ 323 ሺ 294 ሄክታር መሬት በአዝዕርት ሰብሎች ለማልማትና ከዚህም ሰባት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማግኘት አቅዶ ሲሠረ ቆይቷል:: በምርት ዘመኑ በክልሉ 322 ሺ 911 ሄክታር መሬት በዘር መሸፈን ተችሏል::

ክልሉ በማሳ ሽፋን ከዕቅድ በላይ መሄድ የሚችልበት ዕድል እንደነበረው ጠቅሰው፣ በወርሃ ነሐሴ ዝናብ ከመቋረጡ ጋር በተያያዘ በተገቢው መንገድ ማሳዎችን በዘር መሸፈን እንዳልተቻለ ምክትል የቢሮ ኃላፊው ይናገራሉ:: ከዝናቡ መቋረጥ ባለፈም ከተዘሩት ሰብሎች ውስጥ ስምንት ሺ ሄክታር ያህል ሰብል መበላሸቱንና በሌላ ሰብል እንዲተካ መደረጉን ገልጸዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ በመኸር ወቅት በዋናነት 10 ሺ ኩንታል ምርጥ ዘር ለማቅረብ የታቀደ ሲሆን፤ የተመሰከረለት ዘርና ምርጥ ዘር ተደምሮ 15 ሺ 765 ኩንታል ምርት ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል:: 36 ሺ 356 ሄክታር መሬት የሚሸፍን የአፈር ማዳበሪያ ጥቅም ላይ ውሏል::

ከአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና ስርጭት ጋር ተያይዞ በሀገሪቱ ያሉት ችግሮች እንዳሉ ሆነው 72 ሺ ሄክታር መሬት የሚሸፍን የአፈር ማዳበሪያ ለማቅረብ ተቅዶ እንደነበር አስታውሰዋል:: የዩሪያ ማዳበሪያ በየጊዜው እየታየ የሚጨምር መሆኑን ወይም በማሳ ላይ ተጨምሮ ያልተጠናቀቀ መሆኑን ጠቅሰው፣ ጥቅም ላይ የዋለው 36 ሺ 356 ሄክታር መሬት የሚሸፍን የዩሪያ ማዳበሪያ ቁጥሩ ሊጨምር እንደሚችል ነው ያስረዱት::

በበልግ ወቅትም እንዲሁ በክልሉ ሰፊ ማሳ በዘር የተሸፈነ መሆኑን የጠቀሱት አቶ አሸናፊ፤ እንደ ክልል 325 ሺ 556 ሄክታር መሬት በዘር መሸፈን እንደተቻለ ተናግረዋል:: ይህም በመኸር ወቅት በዘር ከተሸፈነው ጋር ሲደመር በአጠቃላይ 650 ሺ ሄክታር አካባቢ የሚደርስ ማሳ በአዝዕርት ሰብል ብቻ የተሸፈነበት አግባብ ስለመኖሩ አመላክተዋል::

የሆልቲካልቸርና ቋሚ ሰብሎች ሲጨመሩ ደግሞ በበልግና በመኸር ወቅቶች በሰብል የተሸፈነው መሬት ወደ ዘጠኝ መቶ ሺ ሄክታር መሬት የሚደርስ መሆኑን የጠቀሱት አቶ አሸናፊ፤ በዚህም በክልሉ አጠቃላይ በአዝዕርት ሰብሎችና በሆልቲካልቸር ምርቶች ጭምር በዓመት እስከ ዘጠኝ መቶ ሺ ሄክታር መሬት የሚሸፈን እንደሆነ ተናግረዋል:: በመሆኑም በሁለቱ የምርት ወቅቶች በጠቅላላው ከ85 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ከክልሉ የሚገኝ መሆኑን አመላክተዋል::

የምርት አሰባሰብን አስመልክቶ አቶ አሸናፊ ሲያብራሩ፤ በበልግና በመኸር የተገኘው ምርት በተመሳሳይ ወቅት የሚሰበሰብበት ጊዜ ስለመኖሩ ጠቅሰው፤ ከመስከረም ወር ጀምሮ ባሉት ተከታታይ ጊዜያት ምርት እንደሚሰበሰብ ነው ያስረዱት::

እሳቸው እንዳሉት፤ በበልግ ወቅት ከተመረተው ምርት 11 ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይገኛል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን፤ በመኸር ወቅት በዘር ከተሸፈነው ማሳ ደግሞ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል:: በድምሩም በ2015/16 ከአዝዕርት ሰብሎች ብቻ 18 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይገኛል ተብሎ የሚጠበቅ መሆኑን ተናግረዋል::

አቶ አሸናፊ እንዳሉት፤ በክልሉ በየዓመቱ የሚገኘው ምርት ለገበያ በሚቀርብበት ጊዜ በሀገሪቱ ገበያ ላይ ከፍተኛ ድርሻ አለው:: ክልሉ ከአዝዕርት ሰብሎች በተጨማሪ በሆርቲካልቸር ዘርፍ ዕምቅ አቅም አለው:: በተለይም ሙዝ፣ አቦካዶና ማንጎ በአካባቢው በስፋት ይመረታሉ:: የክልሉ የሙዝ፣ የአቦካዶና የማንጎ ምርት ከአካባቢው ገበያ አልፎ ለማዕከላዊ ገበያ እየቀረበ የሚገኝ ሲሆን፤ ይህም ክልሉ በኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ድርሻ ከፍተኛ እንዲሆን አድርጎታል ነው ያሉት::

**በበልግ ወቅት** በዘር ከተሸፈነው መሬት 11 ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ኩንታል እንዲሁም በመኸር ወቅት በዘር ከተሸፈነው መሬት ደግሞ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በምርት ዘመኑ በክልሉ ያጋጠሙ ችግሮች ስለመኖራቸው አቶ አሸናፊ ጠቅሰዋል:: በተለይም የዝናብ እጥረትና ከዝናብ እጥረቱ ጋር ተያያዥ የሆኑ የበሽታና የተባይ መከሰት አጋጥሞ እንደነበር አስታውሰው፣ በክልሉ የተከሰተው የበሽታና የተባይ ክስተት በወረርሽኝ ደረጃ አለመሆኑን ተናግረዋል:: ይህም በሰብል ላይ ያደርስ የነበረውን የጉዳት መጠን የቀነሰው መሆኑን ገልጸዋል:: ችግሩ የተከሰተውም በቡቃያ ወቅት መሆኑን አስታውቀው፣ በዚህ ወቅት የተከሰተውን በሽታና ተባይ የመከላከል ሥራ መሠራቱን ገልጸዋል:: አሁንም በቡቃያ ደረጃ ባሉት ሰብሎች ላይ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል::

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በተፈጥሮ የታደለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከበልግና ከመኸር ወቅት በተጨማሪ በመስኖ ልማት ሥራስ ምን ምን ተሠራ፤ ምንስ ውጤት ተገኘ ስንል ላነሳነው ጥያቄ እንደ ክልል በቅርቡ የበጋ መስኖ ስንዴ እና ሆርቲካልቸር ልማት ታቅዶ እየተሠራ መሆኑንም አቶ አሸናፊ ይናገራሉ:: በተለይም በበጋ መስኖ ስንዴ ላይ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በክልሉ በስድስት ዞኖች ማለትም ከፋ ዞን፣ ዳውሮ ዞን፣ ቤንች ሸኮ ዞን፣ ኮንታ ዞን፣ ሸካ ዞንና ምዕራብ ኦሞ ዞን ላይ የበጋ መስኖ ሥራ መጀመሩን ነው የጠቀሱት::

በበጋ መስኖ ከሰባት ሺ 140 ሄክታር በላይ መሬት በስንዴ ሰብል ለመሸፈን አቅደው እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህ መጠን ከክልሉ ካለው እምቅ አቅም ጋር ሲነጻጸር እጅግ ዝቅተኛ ነው ይላሉ:: ለዚህም ዋነኛ ችግር የሆነው በክልሉ የመስኖ መሠረተ ልማት አለመልማቱ ዋነኛ ችግር መሆኑን ተናግረው፣ የመስኖ መሠረተ ልማት ባልተሟላበት ደግሞ በበጋ መስኖ አዝዕርቶችንም ሆነ የሆርቲካልቸር ልማት ማካሄድ አዳጋች መሆኑን ተናግረዋል::

ይሁንና በቀጣይ ክልሉ ሙሉ አቅሙን ተጠቅሞ በበጋ መስኖ የተለያዩ ምርቶችን ማምረት እንዲችል አስፈላጊዎቹ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውን ነው አቶ አሸናፊ የተናገሩት፤ በዚህም ለልማት አስፈላጊ የሆኑ ፓምፖችን ጨምሮ የማሳ ልየታ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን አቶ አሸናፊ ገልጸዋል:: ከዚሁ ጋር በተያያዘም የጋራ የንቅናቄ መድረክ በመፍጠር ለአርሶ አደሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎች እንደሚሰጡ ጠቅሰው፣ በቀጣይ ክልሉ ሙሉ ለሙሉ ወደ በጋ መስኖ ልማት እንደሚገባም ጠቁመዋል::

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ሦስት ሺ ሄክታር በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬት እንዳለው የጠቀሱት አቶ አሸናፊ፤ ክልሉ በመስኖ ሊለማ የሚችል ሰፊ የመሬት ሽፋን ቢኖረውም በአካባቢው የመስኖ መሠረተ ልማት የተሟላ ባለመሆኑ የበጋ መስኖን በሙሉ አቅሙ መጠቀም አልቻለም ብለዋል:: ከመስኖ መሠረተ ልማቶች በተጨማሪም የመስኖ ልማት ሊከናወን በሚችልባቸው አካባቢዎች የመንገድ ችግር መኖሩን ጠቅሰው፤ በተለይም በመስኖ ሊለማ የሚችል ሰፋፊ መሬት ባለበት በኦሞ ዞን አካባቢ መንገድ አለመኖሩን ነው ያመላከቱት::

እሳቸው እንዳሉት፤ ከኦሞ ወንዝ በተጨማሪም በሸካ፣ ዳውሮና በሌሎች አካባቢዎች ጭምር ትላልቅ ወንዞች ይገኛሉ:: አካባቢዎቹ የበጋ መስኖ ሊለማባቸው የሚችሉ ሰፋፊ መሬቶች አላቸው:: ነገር ግን ወደ አካባቢው ለመድረስ የመንገድ እና የመስኖ አውታሮች አልተዘረጉም:: ለዚህም የክልሉ መንግሥት ከፌዴራል መንግሥት ጋር በመሆን መሠረተ ልማቱን ለማሟላት ጥረት እየተደረገ ይገኛል::

ይሁንና ለጊዜውም ቢሆን በአካባቢው በሚገኙ የመሠረተ ልማት አውታሮችና በባህላዊ መስኖ ተጠቃሚዎች በፓምፖች በመታገዝ ከባዶ በመነሳት የበጋ መስኖ ስንዴ እየለማ ነው ያሉት አቶ አሸናፊ፤ በተለይም በ2015/16 የተሻለ ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል::

እሳቸው እንዳሉት፤ ባለፈው ዓመት በበጋ መስኖ 3500 ሄክታር መሬት በዘር የተሸፈነ ሲሆን፣ አሁን ግን ይህን አሀዝ በእጥፍ ለማሳደግ እየተሠራ ነው:: በቀጣይም የመንገድ መሠረተ ልማቶች ሲሟሉና የመስኖ አውታሮች ተዘርግተው ምቹ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ አሁን ካለው በእጥፍ በመቶ ሺ የሚቆጠር ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ስንዴና ሌሎች ሰብሎች ሊለሙ እንደሚችሉ ነባራዊ ሁኔታው ያሳያል::

ለግብርና ሥራው ፈታኝ ከሆኑ ችግሮች መካከል ማዳበሪያ አንዱ እንደሆነ የጠቀሱት አቶ አሸናፊ፤ የማዳበሪያ ችግር እንደ ሀገር ያለው እንዳለ ሆኖ በአሁኑ የዘር ወቅት ማዳበሪያን በወቅቱ ለማቅረብ ዝግጅት ተደርጓል ብለዋል:: ማዳበሪያ በክረምት የተገዛ መሆኑን ጠቅሰው፣ በጊዜው የሚደርስ እንደሆነ ያላቸውን ተስፋ ተናግረዋል::

ሌላው በክልሉ በዋናነት ከሚጠቀሱ ችግሮች መካከል ከፍተኛ የሆነ የዝናብ መጠን ያለበት ክልል መሆኑን የጠቀሱት አቶ አሸናፊ፤ በዚህ የተነሳ በክልሉ የአፈር አሲዳማነት ችግር እየተከሰተ ነው ብለዋል:: ለዚህም አፈሩ በኖራ እየታከመ ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ ከፌዴራል መንግሥት ጋር በጋራ በመሆን እየተሠራ ስለመሆኑ ተናግረዋል:: በክልሉ አልፎ አልፎ የሚከሰተው ተባይና በሽታን አስመልክቶም በወረርሽኝ መልክ የሚታይ እንዳልሆነ ያነሱት አቶ አሸናፊ፤ በ2014/15 በወረርሽን መልክ የተከሰተ በሽታና ተባይ አለመኖሩን ተናግረዋል::

በክልሉ አረሞችን በሰው ኃይል በእጅ የማረም ልምድ እንዳለም ጠቅሰው፣ አሁን ግን የተቀናጀ የአረምና በሽታ ቁጥጥር የሚል ሥርዓት ተዘርግቶ እየተሠራ መሆኑንም ተናግረዋል:: በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ከፍተኛ የንብ መንጋ ስለመኖሩ ጠቅሰው፣ ለዚህም ሲባል ክልሉ እንደ ሌሎች ክልሎች ኬሚካል ላይ ትኩረት የማያደርግና ኬሚካል የማይጠቀም መሆኑን አመላክተዋል:: ለባለሙያዎች ሥልጠና በመስጠት አረሞችን በእጅ የማረም ሥራ በስፋት እየተሠራ እንደሆነና ይህም የመሬቱን ለምነት እንዲሁም የአካባቢውን ባዮ ዳይቨርሲቲ ጠብቆ ለማቆየት ጠቃሚ እንደሆነ አስረድተዋል::

በክልሉ የተፈጥሮ ማዳበሪያን መጠቀም እየተለመደ መሆኑን የገለጹት አቶ አሸናፊ፤ በተለይም በተያዘው የመኸር ወቅት የተፈጥሮ ማዳበሪያን ለጥራጥሬ ሰብሎች በስፋት መጠቀም መቻሉን ተናግረዋል:: እሳቸው እንዳሉት፤ ባዮፈርቲላይዘር የሚባል በፋብሪካ የሚዘጋጅ የተፈጥሮ ማዳበሪያ በክልሉ አገልግሎት ላይ እየዋለ ይገኛል:: ይህም ለሰብሎቹ የዩሪያ ፍላጎትን ሊያሟላ የሚችል በመሆኑ በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውል እየተደረገ ነው::

ከዚህ በተጨማሪ ለሆርቲካልቸር ሰብሎች የኮምፖስት ዝግጅት በአርሶ አደር ደረጃ በስፋት እየተዘጋጀ እንደሆነ ያመላከቱት አቶ አሸናፊ፤ «አንድ አርሶ አደር አንድ የኮምፖስት ጉድጓድ» በሚል መርህ የጋራ ግንዛቤ በመፍጠር በስፋት እየተሠራበት መሆኑን አስታውቀዋል:: በቀጣይም አርሶ አደሩን የማስተማርና ግንዛቤውን የማሳደግ ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረው፣ በአሁኑ ወቅትም እንደ ክልል ቡናን ጨምሮ አንዳንድ ሰብሎች ሙሉ ለሙሉ በኮምፖስት እየለሙ እንደሆነ አቶ አሸናፊ አስታውቀዋል:: ይህ ጅማሮ በሌሎች ሰብሎችም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል::

# የዩኒቨርሲቲዎች ልየታ መርሐግብር- የዓመቱ ቁልፍ ተግባር

**ወግርማ መንግሥቴ**

የሀገራችን የትምህርት ጉዳይ ሁሌም ቢሆን የመነጋገሪያ አጀንዳ ነው፡፡ ከታች እስከ ላይ እንዳነጋገረ አለ። በሁሉም የትምህርት እርከኖች ላይ እንዳወያየ ነው። በሁሉም የትምህርት ይዘቶች ላይ ውዝግብ ነበር፤ አሁንም አልተፈታም - አለ።

በተለይም፣ የትምህርት ጥራት ጉዳይ እጅግ አሳሳቢ እየሆነ ከመምጣቱ የተነሳ «የኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ጥራት ምክር ቤት» የሚል እስከ ማቋቋም ድረስ ተሄዶ እንደነበር እናስታውሳለን። ዛሬ ምን ደረጃና ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ግልፅ አይደለም እንጂ፣ በወቅቱ እንደተገለፀው ከሆነ የምክር ቤቱ ዓላማና ተልዕኮ ግሩምና አሻጋሪ ይመስል ነበር።

ይህ በዓይነቱ ልዩ የሆነ፣ ለትምህርት ጥራትና አግባብነት ጉልህ አስተዋፅኦ ያለው፤ ከሥርዓተ ትምህርት ቀረጻ ጀምሮ ተማሪዎችን ለማብቃት በጋራ መሥራት ድረስ እንደሚዘልቅ ተገልፆለት የነበረው ተቋም (የኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ጥራት ምክር ቤት) ከ200 በላይ የሙያ ማኅበራትን ያካተተ ሲሆን በትምህርት ጥራትና አግባብነት ላይ አተኩሮ የሚሠራ እንደሆነም በምስረታው ወቅት ተገልፆ ነበር። ይሁን እንጂ፣ አሁን አሁን ስለዚህ ምክር ቤት እየተሰማ ያለ ምንም ነገር የለም።

ለውጡን ተከትሎ ኢትዮጵያ ሳይንስንና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን በኃላፊነት የሚመራና የሚያስተዳድር ተቋም (የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር) ምስረታ ተቋሙ በፍጥነት ወደ ተግባር በመግባት በርካታ ሥራዎችን ሲያከናውን የነበረ ሲሆን፣ አንዱም የልየታ ሥራ (Higher Education Differentiation) እንደነበር የምናስታውሰው ነው። በተለይም እንደ አንድ የሚዲያ ተቋም ይህ ጋዜጣም አስፈላጊውን ትኩረት በመስጠት ሰፊ ሽፋን ሰጥቶ የዘገበው መሆኑም የሚረሳ አይደለም። አሁን፣ ጊዜው ደርሶ መርሐ ግብሩ ወደ መሬት የመውረጃው ወቅት እንደመሆኑ መጠን፣ በጉዳዩ ላይ የተወሰነ ወቅታዊ ሃሳብ በማከል ሂደቱን ማሳየት ይገባል፡፡

በወቅቱ (ጥቅምት፣ 2013 ዓ.ም) የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር (አሁን ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር ተዋህዷል) ሚኒስትር በነበሩት ዶ/ር ሳሙኤል ኡርቃቶ ዩኒቨርሲቲዎቹን በትኩረት መስክ መለየት (Differentiation ይሉታል) የሀገሪቱን ብልጽግና ለማሳካት እንደሚረዳ ተገልፆ ነበር፡፡ «ተቋማቱ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ በመወጣት አርአያ ሆነው የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ የሚፈልገውን ተወዳዳሪ የሰው ኃይል ማፍራት» ያለባቸው መሆኑም እንደዚያው።

የዚሁ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ የነበሩት ዶ/ር ሙሉ ነጋ በበኩላቸው የዩኒቨርሲቲዎች ልየታ ዋና ዓላማ ዩኒቨርሲቲዎቹን ለማበላለጥ ሳይሆን ከነበራቸው የትኩረት አቅጣጫ በመነሳት የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ መሆኑን ተናግረው ነበር።

በዚህ በልየታ አሠራር መሠረትም በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ 7 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአምስት የትኩረት መስኮች የተለዩ ሲሆን፥ በዚህም የምርምር፣ አጠቃላይ፣ የአፕላይድ ሳይንስ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እና የቴክኒካል ዩኒቨርሲቲዎች ተብለው መመደባቸውም አይዘነጋም።

በትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ጥናት ውጤት መሠረት 8 የምርምር፣ 15 የአፕላይድ ሳይንስ፣ 2 የሳይንስና ቴክኖሎጂ እና ቀሪዎቹ 21ዱ የአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲ ተብለው መለየታቸውም ይታወቃል።

በምርምር ዩኒቨርሲቲነት የተመደቡ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትም፥ አዲስ አበባ፣ አርባ ምንጭ፣ ባህርዳር፣ ጎንደር፣ ሀረማያ፣ ሀዋሳ፣ ጅማ እና መቐለ ናቸው። አክሱም፣ አምቦ፣ አርሲ፣ አሶሳ፣ ደብረብርሃን፣ ደብረማርቆስ፣ ዲላ፣ ድሬዳዋ፣ ጅግጅጋ፣ ኮተቤ፣ ሰመራ፣ ወላይታ ሶዶ፣ ወልቂጤ፣ ወለጋ እና ወሎ ዩኒቨርሲቲ የአፕላይድ ዩኒቨርሲቲዎች ተብለዋል።

አዲግራት፣ ቦንጋ፣ ቦረና፣ ቡሌሆራ፣ ደባርቅ፣ ደብረታቦር፣ ድምቢዶሎ፣ ጋምቤላ፣ እንጅባራ፣ ጂንካ፣ ቀብሪደሃር፣ መዳወላቡ፣ መቅደላአምባ፣ መቱ፣ ሚዛን ቴፒ፣ ኦዳ ቡልቱም፣ ራያ፣ ሰላሌ፣ ዋቸሞ፣ ወራቤ እና ወልዲያ ዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ አጠቃላይ ዩኒቨርሲቲዎች ሆነዋል። የአዳማ ሳይንስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ እና የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲነት ተለይተዋል።

በቴክኒካል ዩኒቨርሲቲ ስር ደግሞ የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ተመድቧል።

በተደጋጋሚ እንደተገለፀው፣ ይህንን ውሳኔ ለማሳለፍ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሌሎች ሀገራትን ተሞክሮ መሠረት በማድረግ ጥናቱን አካሂዷል። ይህንንም የልየታ ምክረ ሃሳብ በተቻለ ፍጥነት ወደ ተግባር ለመቀየር ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተከታታይ ውይይቶች መደረጋቸውም እንዲሁ በወቅቱ ተገልፆ እንደነበር ይታወቃል።

ባለፈው አመት «በሀገሪቱ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ከሚቀጥለው በጀት ዓመት አንስቶ የሚያቀርቧቸው አዳዲስ የግንባታ ፕሮጀክቶች የሚጸድቁላቸው፣ ትምህርት ሚኒስቴር ከሰጣቸው የልህቀት ማዕከልነት ልየታ ጋር ከተስማማ ብቻ» ነው የሚል የትምህርት ሚኒስቴርን አቋም መስማታችን በራሱ የሚነግረን እውነት ቢኖር የልየታ መርሐግብሩ (ተቋማቱን በልህቀት ማዕከልነት መመደቡ) ወደ ኋላ የማይመለስ መሆኑን ነውና የመርሐግብሩን ውጤታማነት ከወዲሁ እንድንጓጓለት ያደርገናል።

ይህ የልየታ መርሐግብር ታስቦበት የተገባበት ስለመሆኑ ሌላው ማሳያ (ደረጃ) «ታንዳርድ» የተሠራለት (ያለው) መሆኑ ሲሆን፤ ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ለልህቀት ማዕከልነት የተቀመጠውን መስፈርት(ስታንዳርድ) ለማሟላት የሚቀራቸውን መሠረተ ልማት ለመለየት፣ የመሠረተ ልማት ልየታ ለማካሄድ ይቻል ዘንድ ቡድን መዋቀሩን መስማታችን፤ ለተግባራዊነቱም በሚኒስቴሩ የአስተዳደርና መሠረተ ልማት ዘርፍ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በኃላፊነት መመደቡና የመሳሰሉት የሚነግሩን ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት የተሰጠው መሆኑን ነው።

### የትኩረት መስኮቹ ከነማብራሪያዎቻቸው፤

ከላይ፣ የቀድሞው የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በ2012 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓት ልየታ (Higher Education Differentiation) በሀገሪቱ የሚገኙ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎችን በአምስት ዋና ዋና የትኩረት መስኮች የምርምር፤ አፕላይድ ሳይንስ፣ ኮምፕሬሄንሲቭ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ እንዲሁም ቴክኒካል በሚል መለየቱ የሚታወስ ሲሆን፤ እንደሚከተለውም አብራርቷቸው (www.moshe.gov.et www.facebook.com/SHE.Ethio) ነበር።

### 1. የምርምር ዩኒቨርሲቲ

በዚህ ምድብ ስር የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች በድኅረ-ምረቃ ትምህርት እና ምርምር ላይ ያተኩራሉ፤ ከቴክኖሎጂ ሽግግር እና ከድኅረ-ምረቃ ሥልጠና ጎን ለጎን በተለይ የምርምር አቅምን፣ የምርምር አፈፃፀምን እና የመምህራን ምርምር ውጤታማነትን ማሳደግ ላይ በትኩረት ይሠራሉ።

### 2. አፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲ

የአፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲዎች ሙያ-ተኮር የትምህርት መርሐግብሮች ያሏቸው ሲሆኑ፣ በእነዚህ ተቋማት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች የንድፈሃሳብ ዕውቀታቸውን እንዴት ተግባር ላይ ማዋል እንዳለባቸው እውቀት ይዘው ይወጣሉ፡፡ በብሔራዊ እና ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ውስጥ የተለያዩ ፕሮጀክቶች፣ የሥራ ምደባዎች እና የሥራ ላይ ልምምዶች በእነዚህ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የሚሰጡ የዲግሪ መርሐ-ግብሮች አካላት ናቸው፡፡

### 3. አጠቃላይ ዩኒቨርሲቲ

በዚህ ምድብ ስር ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች አጠቃላይ የማስተማር፣ ምርምር እና የማኅበረሰብ ተሳትፎ የሚከናውንባቸው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ናቸው። የዶክትሬት፣ የማስተርስ እና የመጀመሪያ ዲግሪ መርሐግብሮችን የሚያካትቱ ሲሆን፣ ማስተማር እና ምርምር ላይ በተመጣጠነ መልኩ ይሠራል።

### 4. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎች

የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲና የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲዎችን የሚያቅፍ ይሆናል።

### 5. የቴክኒካል ዩኒቨርሲቲ፤

የኢትዮጵያ ቴክኒካል ዩኒቨርሲቲዎች በዚህ ስር የሚካተቱ ናቸው፡፡

በወቅቱ ከተገኘ መረጃ ለመረዳት እንደሚቻለው፣ በየዩኒቨርሲቲዎቹ የሚሰጡ የትምህርት መስኮችን በተመለከተ ባጠቃላይ ባሉ 47 ዩኒቨርሲቲዎች ከ200 በላይ የቅድመ-ምረቃና ከ450 በላይ የሁለተኛ ዲግሪ እንዲሁም ከ200 በላይ የሦስተኛ ዲግሪ የትምህርት መስኮች ይሰጣሉ።

### አሁን ምን እየተደረገ ነው?

በትምህርት ሚኒስቴር የአካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ሥራ አስፈፃሚ የሆኑት ዶ/ር ኤባ ሚጀና ሰሞኑን ከመገናኛ ብዙሃን ጋር በጽሕፈት ቤታቸው ባደረጉት ቆይታ ወቅት እንደገለፁት፣ በተጀመረው ዓመት የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ለተመደቡበት የትኩረት መስክና ተልዕኮ የዝግጅት ሥራ ቅድሚያ ይሰጣሉ፡፡ በ10 ዓመታት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ወደ ትኩረት መስክና ተልዕኮ እንዲሸጋገሩ የትግበራ ፍኖተ ካርታ ተዘጋጅቶ የመጀመሪያው ምዕራፍ ሥራ ተጀምሯል።

የትምህርት ሚኒስቴር የዘርፉን ስብራቶች ለማስተካከል ከወሰዳቸው እርምጃዎች አንዱ የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎችን በትኩረት መስክና በተልዕኮ ተለይተው እንዲሠሩ ማድረግ መሆኑን የሚናገሩት ዶ/ር ኤባ፣ በተለይ የተማሪዎችን ዕጣ ፈንታ በተመለከተ ለአዲስ ዘመን እንደገለፁት «የነበሩት (ነባሮቹ) በጀመሩት ይቀጥላሉ፤ በዚያውም ያጠናቅቃሉ። አዲስ ገቢዎችም በአዲሱ የትኩረት መስክ በመመዝገብ ትምህርታቸውን መከታተል ይጀምራሉ።» በማለት መልሰዋል።

በቅርቡ አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ሳውላ ካምፓስ በቅድመ ምረቃ መርሐግብር ያሠለጠናቸውን 91 ወንድና 58 ሴት በድምሩ 149 የ6ኛ ባች ተማሪዎች ለ2ኛ ዙር መስከረም 13/2016 ዓ.ም ባስመረቀበት ወቅት በክብር እንግድነት የተገኙት ዶ/ር ኤባ «የትምህርት ጥራትን በማስጠበቅ ብቁ እና በቂ የሰው ኃይልን ማፍራት እንዲሁም የዘመኑን ዕውቀት ተጠቅሞ ቴክኖሎጂን መፍጠር፣ ማሻሻል ብሎም ማላመድ ወሳኝ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ሀገራችን ያለችበትን ነባራዊ ሁኔታ ለመቀየር የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የለውጥ ሃሳቦችን በማፍለቅና በመተግበር አርአያ የሚሆኑ ዜጎችን ማፍሪያ፣ የዴሞክራሲያዊ አስተሳሰቦችና ቴክኖሎጂዎች መፍለቂያ እንዲሁም የባሕላዊ እሴቶች ማጎልበቻ ማዕከላት እንዲሆኑ ማድረግ አማራጭ የሌለው መፍትሔ መሆኑን» መናገራቸው ለአመታት በችግር ተተብትቦ የቆየው የትምህርቱ ሴክተር ከታሰረበት እየተፈታ ይሆን የሚል ጥያቄንም የሚያጭር ብቻ ሳይሆን፣ የሀገራችን መፃኢ ዕድል ብሩህ ይሆን ዘንድ ከወዲሁ የሚያመላክት ይመስላል።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በርካታ ሪፎርሞች (ለውጦች) የተካሄዱ ሲሆን፣ ከ2012 ትምህርት ዘመን ጀምሮ በዩኒቨርሲቲ ትምህርት 3 ዓመት የነበረው ዝቅተኛ የቅድመ ምረቃ ፕሮግራም ቆይታ ወደ 4 ዓመት ማደጉ (ወይም፣ ወደነበረበት መመለሱ) አንዱ ነው።

ለትምህርት ጥራት ሲባል ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ለድህረ ምረቃና ሦስተኛ ዲግሪ የሚቀበሏቸውን ተማሪዎች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አማካኝነት ትምህርት ሚኒስቴር የሚዘጋጀውን ፈተና በመውሰድ ማለፍ የሚጠበቅባቸው ሲሆን፣ ይህ ዘንድሮ የሚጀመር መሆኑን መሪ ሥራ አስፈፃሚው ዶ/ር ኤባ ለአዲስ ዘመን ገልፀዋል፡፡ «ይህ ብቻም አይደለም፣ ከዚህ አጠቃላይ ፈተናም በኋላ የትምህርት ክፍሎች የየራሳቸውን ፈተና በማውጣት የሚፈትኑና ያለፉትን የሚቀበሉ ይሆናል» ሲሉም አክለዋል።

በአጠቃላይ፣ የዛሬው ትኩረታችን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በትኩረት መስክ ልየታ ሥራ (Higher Education Differentiation) ላይ ሆነ እንጂ በትምህርቱ ዘትርፍ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ፤ ለውጦችም እየታዩ፤ በተለይም በባለ ድርሻ አካላት ዘንድ መነሳሳቶች እየተፈጠሩ ስለመሆናቸው በስፋት እየታየ ሲሆን፤ መገናኛ ብዙኃንም እነዚህን ለውጦች ወደ ሕዝብ ሲያደርሱ መቆየታቸው ይታወቃል። ከነዚህ መካከልም ይህ የልየታ መርሐግብር አንዱ እንደመሆኑ መጠን፣ ሁሉም ማስትሬትና ዶክትሬት ሰጪ፣ ሁሉም ኬሚስትሪ አስተማሪ ከመሆን ተላቅቆ፤ ሁሉም በሕግ አስመራቂ ከመሆን ወጥቶ፤ ሁሉም ካልተገባ ፉክክርና ግርግር ወጥቶ የራሱ የሆነ ትኩረትና ተልዕኮ ኖሮት - - - ዘንድሮ ወደ ተግባር መግባቱን ስንገልፅ ለመልካም አፈፃፀሙም መልካሙን ሁሉ እየተመኘን ነው።

# ወቅታዊ

## ‹‹ምክክሩ የሚሠራው ወቅታዊ ስሜቶችን ለማረጋጋት ሳይሆን የተፈጠሩበትን ገፊ ምክንያቶች ለይቶ መሠረታዊ መፍትሔ ለማምጣት ነው››

-አቶ ጥበቡ ታደሰ
የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ቃል አቀባይ



ፎቶ: በገበቡ ገብሬ

አስቴር ኤልያስ

**የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ የታወጀበት አንዱ ምክንያት መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ አካታች ሀገራዊ ምክክሮችን በማካሔድ የተሻለ ሀገራዊ መግባባትን ለመገንባት በማስፈለጉ ነው፡፡ በሒደትም የመተማመንንና ወሳኝ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ተቀራርቦ የመሥራት ባህልንም ለማጎልበት ታስቦ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ ሲያከናውን የነበረውን ሥራ ሰሞኑን አንዱ ባለድርሻ አካል ለሆነው መንግሥት ገለጻ ማድረጉ ይታወቃል፡፡ ኮሚሽኑ በእስካሁኑ ሒደት ስለሠራቸው ሥራና በቀጣይ ስለሚያከናውነው ተግባር አስመልክቶ አዲስ ዘመን ከኮሚሽኑ የሚዲያ ኮሙኒኬሽንና አጋርነት ዘርፍ አስተባባሪ እና የኮሚሽኑ ቃል አቀባይ ከሆኑት ከአቶ ጥበቡ ታደሰ ጋር ያደረገውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተው አጠናቅሮ አቅርቧል፡፡ መልካም ንባብ፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- በቅርቡ ኮሚሽኑ የደረሰበትን የሥራ ሒደት ለመንግሥት አቅርቧል፤ የነበረው ግብረመልስ ምን ይመስል ነበር?**

**አቶ ጥበቡ፡-** ሰሞኑን ከመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ጋር ኮሚሽኑ ውይይት ነበረው:: ከዚህ የተነሳ ኮሚሽኑ ለመንግሥት ሪፖርት አቀረበ ተብሎ ሲዘገብ አስተውለናል:: ነገር ግን ያቀረበው ለመንግሥት ሪፖርት አይደለም:: ምክንያቱም ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው:: ስለሆነም ሪፖርት የሚያቀርበው ለኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች እና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነው እንጂ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለካቢኔያቸው የማቅረብ ኃላፊነት የለበትም:: ስለዚህ አንዱ መታረም ያለበት ጉዳይ ነው ብለን እናምናለን:: መንግሥት እንደ አንድ ባለድርሻ አካል የሀገራዊ ምክክሩ አካል ነው:: ለምሳሌ መምህራን፣ ሲቪል አካላት፣ ፖለቲከኞችና ሌሎችም እንደሆኑት ሁሉ መንግሥትም አንዱ ባለድርሻ አካል ነው:: ኮሚሽኑም ከእነዚህ ባለድርሻ አካላት ጋራ በጋራ የሚሠራቸው በርካታ ሥራዎች አሉት::

ልክ ከሌሎቹ ባለድርሻ አካላት ጋር እንደምናደርገው ውይይት ከመንግሥትም ጋር በተካሄደው ውይይት አንዳንድ የሚነሱ ጥያቄዎችን ተቀብሎ ኮሚሽኑ ማብራሪያዎችን ሰጥቷል:: ከፍተኛ አመራሩም እስካሁን የተሠሩ ሥራዎችን አድንቀው ኮሚሽኑ ጥሩና መልካም ጅምር ላይ እንዳለ ጠቅሰው ሥራውን አጠናክሮ እንዲቀጥል ግብረ መልስ ሰጥተዋል:: ኮሚሽኑ በሚያደርገው ሥራ እንደ አንድ ባለድርሻ አካል መጫወት ያለበትን ሚና ለመጫወት ቁርጠኛ መሆኑን ገልጿል::

**አዲስ ዘመን፡- እንደ አንድ ባለድርሻ አካል ከመንግሥት ጋር ባደረጋችሁት ውይይት የጠበቃችሁት ምላሽ እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ጥበቡ፡-** እንደተጠበቀው መልካም ነው:: መንግሥት ሲባል ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ብቻ ሳይሆኑ እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ መንግሥት በፌዴራልም በክልልም ደረጃ ያሉ የሥራ ኃላፊዎች ናቸው:: ስለዚህ ባከናወንናቸው ሒደቶች በየደረጃው ያሉ የመንግሥት አካላት እስካሁን በታየው ትብብራቸው በጣም አበረታች ነው:: መደገፍ ባለባቸው ሁሉ በመደገፍ ላይ ናቸው:: በዚህኛውም መድረክ ላይ የታየው ነገር ተመሳሳይ ነው:: እንዲህ ሲባል የኮሚሽኑ ገለልተኝነትና ነፃነት እንደተጠበቀ ነው:: የተገለጸውም በቀጣይም የሚጠበቅባቸውን ለማድረግ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ኮሚሽኑ በአሁኑ ወቅት እየተገበራቸው ያሉ ሥራዎችና የደረሰበት ውጤት እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ጥበቡ፡-** እስካሁን ከተሠሩ በርካታ ሥራዎች በርካታ ጉዳዮችን ለማከናወን ጥረት ተደርጓል:: እኛ ሥራ የምንሠራው በአራት ምዕራፍ ከፍለን ነው:: የቅድመ ዝግጅት፣ የዝግጅት፣ የሒደትና የትግበራና የክትትል ምዕራፍ በሚል ነው:: አሁን ባለው ሁኔታ የቅድመ ዝግጅቱ እና የዝግጅቱ ምዕራፍ ተጠናቅቆ የሂደት የምንለው ሦስተኛው ምዕራፍ ላይ እንገኛለን:: የቀረን ነገር ቢኖር ወደአራተኛው ምዕራፍ መሸጋገር ነው::

በአሁኑ ወቅት የሠራችሁት ምንድን ለተባለው የተያዘው ዓመት 2016 ዓ.ም እንደመሆኑ የበጀት ዓመቱን እቅድ በመተግበር ጀምረናል:: ከዚህ አኳያ በሀገራዊ ምክክር ላይ የሚሳተፉ ተሳታፊዎች እስካሁን የለየናቸው ክልሎች እንደተጠበቁ ሆነው ተሳታፊዎች ባልተለዩባቸው ቀሪ ክልሎች ለመለየት ትኩረት አድርገን እየሠራን ነው:: እነዚህም የአፋር፣ ሱማሌ፣ አማራ፣ ትግራይ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ ኢትዮጵያና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልሎች ናቸው::

የመጀመሪያ ሥራችን እንደሚታወቀው ተሳታፊ የሚለየው ኮሚሽኑ ብቻ አይደለም:: የተለያዩ ተባባሪ አካላት አሉ:: ስለዚህ በእነዚህ ክልሎች እየሠራን ያለው ተባባሪ አካላትን የመለየት እና የማሰልጠን ሥራ ነው:: ሁለተኛው በሀገራዊ ምክክሩ ዙሪያ ግንዛቤ መፈጠር ስላለበት ኅብረተሰቡ በሚሳተፍበት ጊዜ አውቆና ተረድቶ መሳተፉ ውጤት ስለሚያመጣ ግንዛቤ የሚፈጥሩ በየክልሉ በሚነገሩ የተለያዩ ቋንቋዎች አማካይነት የማዘጋጀትና ተደራሽ የማድረግ ሥራ ትኩረት ሰጥተን የምንሠራው ነው:: ሥራው የሚሠራው ከተለያዩ አካላት ጋር አጋርነትን በመፍጠር ነው:: ስለዚህ የተሳታፊ ልየታ ከምንሠራቸው ክልሎች ያሉ ባለድርሻ እና የመንግሥት አካላት ጋር በመሆን ሥራ እየሠራን ነን::

ሌላው ትኩረት ሰጥተን እየሠራን ያለነው ሥራ ደግሞ እስካሁን ተሳታፊዎችን ከለየንባቸው ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በክልልና በከተማ አስተዳደር ደግሞ የሚሳተፉ የተለያዩ ተሳታፊዎች አሉ:: እነርሱ የሚወከሉት ከተቋማት፣ ከማኅበራትና ከመሳሰሉት ስለሆነ የተወከሉትን ሰዎች የማሰባሰብና መረጃዎችን የማጠናከር ሥራ በተመሳሳይ ጊዜ እየሠራን ነው:: ከዚያ በተጨማሪ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ግንኙነቶቻችንን የማጠናከር ሥራ በትኩረት እየሠራን እንገኛለን::

ሌላው ትኩረት ሰጥተን እየሠራን ያለነው የአጀንዳ ሐሳቦችን የመሰብሰብ ሥራ ነው:: አጀንዳ የሚሰበሰበው ደግሞ አንድም ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ወኪሎቻቸውን መርጠው በእነርሱ በኩል በኮሚሽኑ አስተባባሪነት የሚካሔዱ መድረኮች ላይ ነው:: ከእነዚያ መድረኮች አጀንዳ ይሰበሰባል:: በሌላ መንገድ ደግሞ የአጀንዳ ሃሳቦች የምንሰበስብበት መንገድ በቀጥታ በዚያ መንገድ የመሳተፍ ዕድሉን ያላገኙ ሰዎችም ሆኑ ተቋማት ጭምር የአጀንዳ ሃሳብ አለን በማለት በሚመጡበት ጊዜ በቢሮዎችና በተለያዩ የቴክኖሎጂ አማራጮች የማሰባሰብ ሥራዎችን እየሠራን ነው::

ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች አጀንዳ የምንሰበስብበት መንገድ አሁንም ትኩረት ሰጥተን እየሠራን ያለነው በጥናት ነው:: አንድ ኮሚሽኑ ይህን ለማካሄድ ያለው በዝግጅት ላይ ነው:: ሁለተኛ ነገር ከዚህ ቀደም በተለያዩ ተቋማትና የተለያዩ ግለሰቦች ያካሄዷቸው ጥናቶች ካሉ፤ የሚዲያ ተቋማትም ጭምር ከዚህ በፊት ሲዘግቧቸው የነበሩ ጉዳዮችን በማጥናት ከእነዚያም ደግሞ ጥሩ የአጀንዳ ሃሳቦችን መሰብሰብ ስላለብን እሱንም እንዲሁ ትኩረት ሰጥተን እየሠራን ነው::

በቀጣይ በሚደረገው የአጀንዳ ማሰባሰብ ሂደት ላይና በሀገራዊ ምክክሩ ላይ ያለውን ሒደት የሚያመቻቹ አመቻቾችን እንዲሁ የማብቃትና የመለየት ሥራ ያስፈልጋል:: በተለይ በኢትዮጵያ ከሚገኘው የዩኒቨርሲቲ ተቋማት ጋር በመተባበር ይህን ሥራ ሊሠሩ የሚችሉ በገለልተኝነት፣ በታማኝነትና በግልጸኝነት ሊሠሩ የሚችሉ የተለያዩ ምሁራንንም ጭምር ለማሳተፍ ጥረት እየተደረገ ነው::

በቀጣይ የሚኖሩን ሥራዎች አጀንዳ ማሰባሰቡ፤ መቅረጹና ምክክር ማካሄዱ ናቸው:: እነዚህ በሥርዓት መመራት ያለባቸው ናቸው:: ለምሳሌ ተሳታፊዎቹን የምንለየው ራሱ ኮሚሽኑ በቀረጸው ተሳታፊዎችን የመለያ ሥነ ዘዴ በመጠቀም ነው:: ልክ በተመሳሳይ ሌሎችንም ኹነቶች የምንመራበትን ሥርዓት የመቅረጽ ሥራዎችም እየተሠሩ ነው:: ስለዚህ ከእነዚህ ተጨባጭ ሁኔታዎች ተነስተን የ2016 በጀት ዓመት እቅዳችንን አዘጋጅተን በዚያ እቅድ መሠረት እየተተገበሩ ያሉ ተግባራት ናቸው::

**አዲስ ዘመን፡- የተቀሩት ተሳታፊዎች ያልተለዩባቸው ክልሎች ተሳታፊዎቹን እስከመቼ ለመለየት አቅዳችኋል?**

**አቶ ጥበቡ፡-** የሥራው ባህሪ በራሱ ሒደት ነው:: ሁለተኛ ነገር ደግሞ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ ነው:: ሦስተኛ ነገር ደግሞ ሥራው መሬት ላይ በሚወርድበት ጊዜ አካታችና አሳታፊ መሆን ስላለበት የሚሠራው በሥርዓት ነው:: ስለዚህ ይህን ጉዳይ በዚህ ጊዜ አከናውኗል ማለት የሚያስችል ሁኔታ ላያጋጥም ይችላል:: ምክንያቱም መሬት ላይ በተጨባጭ የምናያቸው አንዳንድ ፈታኝ የሆኑ ሁኔታዎች ስለሚኖሩ ነው:: አሁንም የተፈጠሩ አሉ፤ ምናልባትም ወደፊትም የሚፈጠሩ ይኖራሉ:: ከዚህ አኳያ እኛ በጥቅሉ እየሠራን ያለነው በእቅዳችን መሠረት ነው::

ዋናው ግን እንደ አንድ መነሻ እየሠራን ያለነው በዚህ በ2016 በጀት ዓመት አጋማሽ ላይ ምክክሩን መጀመር ነው:: ምክክሩን እንጀምራለን ካልን ምክክሩ ከመጀመሩ በፊት መከናወን ያለባቸው የያዝናቸው እቀዶች መጠናቀቅ አለባቸው:: ምክክሩን በአጋማሽ ላይ እናካሂዳለን ካልን አሁን ካለንበት ወር ተነስተን በቀሩት ጥቂት ወራት ተሳታፊ ያልለየንባቸውን ክልሎች ለይተን የማጠናቀቅና አጀንዳዎችን ማሰባሰብን መጀመር አለብን:: በተጨማሪም አጀንዳዎቹ መቀረጽም አለባቸው:: ወደምክክሩ የሚገባው ከዚያ በኋላ ነው:: ስለዚህ ሥራዎቹ ከዓመቱ አጋማሽ በፊት ተጠናቅቀው ምክክሩ በዓመቱ አጋማሽ ላይ መጀመር አለበት::

**አዲስ ዘመን፡- በኮሚሽኑ አማካይነት የሚካሔደው ውይይት አሁን በሚታዩ ወቅታዊ ስሜቶች ተጽዕኖ ስር ይወድቃል የሚል ስጋት ይኖር ይሆን?**

**አቶ ጥበቡ፡-** በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ የሚፈጠር ጫና ይኖራል ብለን አንገምትም:: በእቅዳችን መሠረት ሥራችንን ለማከናወን በሚደረግ ጥረት የራሱ ተግዳሮት ሊመጣ ይችላል:: ነገር ግን አንዱ መገንዘብ ያለብን እውነታ አሁን በኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ማድረግ ያስፈለገበት አንዱ ተጨባጭ ምክንያት አሁን በተለያዩ አካባቢዎች ይታያሉ ያልሻቸው ስሜቶች ምናልባትም በእኛ እምነት ከስሜትም ከፍ ያሉ የሀገርን ህልውና የሚፈታተኑ አሳሳቢ ችግሮች አሉ::

አንዱ ምክክሩ በተጨባጭ አስፈላጊ የሚያደርገው በኢትዮጵያ ውስጥ እንደዚህ ዓይነት አውዶች በመኖራቸው ነው:: ስለዚህ እዚህም እዚያም የሚታዩ ችግሮችን እኛ የምናያቸው ውጤቶች መሆናቸው ነው:: በመሆኑም ሀገራዊ ምክክሩ የሚሠራው ወቅታዊ ስሜቶችን ለማረጋጋትና ለማከም ሳይሆን የተፈጠሩበትን ገፊ ምክንያቶች ለይቶ መሠረታዊ መፍትሔ ለማምጣት ነው::

ከዚህ አኳያ አሁን ላይ የሚታዩ ግጭቶች የተለያዩ ገፊ ምክንያቶች ቢኖሯቸውም ዋንኛው ምክንያት ብለን የምናምነው እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮቻችን ላይ ያሉን አለመግባባቶች ናቸው ወደዚያ የሚያደርሱን:: እነዚህን አለመግባባቶች ደግሞ ለመፍታት የምንጠቀምበት አንዱ አማራጭ የኃይል አማራጭ ይሆንና እንዲህ ዓይነት ነገሮችን ይፈጥራሉ ማለት ነው:: ስለዚህ ከዚህ በመነሳት በሀገር ደረጃ ያሉ መሠረታዊ ጉዳዮቻችን ላይ ያሉ አለመግባባቶችን መፍታት ነው:: ከዚህ አኳያ በየወቅቱ የሚታዩ ነገሮች የእኛ አሠራር ላይ ከጊዜ አኳያ እቅዳችንን ሄድ መለስ እንድናደርገው ያስገድዱን ካልሆነ በስተቀር በራሳቸው የሚፈጥሩት የተለየ ጫና አይኖርም::

ከዚያ በተጨማሪ አንድ መታየት ያለበት ምክክር ኮሚሽኑም ሆነ አዋጁም ጭምር መጨረሻ ላይ እንዲያሳካቸው ከሚፈለጉት ዓላማዎች መካከል አንዱ የምናየው ወቅታዊ ችግሮች ዘላቂ በሆነ ሁኔታ መፍታት የሚያስችልና አስተማማኝ የሆነ ሠላም የሚረጋገጥበትን የፖለቲካና ማኅበራዊ መደላድል መፍጠር ነው:: ስለዚህ ይህንን ዓላማ ይዞ የተንቀሳቀሰ ኮሚሽን ወቅታዊ የሆኑ ችግሮችን ዘላቂ በሆነ ሁኔታ ለመፍታት የሚያስችሉ ሥራዎችን እንዲሠራ ኃላፊነት የተሰጠውና እሱንም ለመተግበር እየተንደረደረ ያለ ተቋም በእነዚህ ሊፈቱ በሚችሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ተጽዕኖ ስር የሚወድቅበት ዕድል ይኖራል ተብሎ አይታሰብም::

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዝሃነት መገለጫው ቢሆንም አንዱ ሌላውን በሚገባ ያውቀዋል የሚል እምነት የሌላቸው አካላት አሉ፤**

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ‹‹ምክክሩ የሚሠራው ወቅታዊ ስሜቶችን...

ከ ገጽ 9 የዞረ

**ይህ ከሆነ ስሥራችሁ እንቅፋት ሲሆን ይችላል ተብሎ ይታሰባል?**

**አቶ ጥበቡ፡-** ለሀገራዊ ምክክሩ ብዝሃነት እንቅፋት ሊሆን የሚችልበት ዕድል የለውም፡፡ ብዝሃነት በራሱ ጸጋ ነው፡፡ እንዴት መያዝ እንዳለብን ያለማወቅ ሁኔታ ነው ችግር የሚፈጥርብን እንጂ ብዝሃነት በራሱ ችግር የለበትም፡፡ ነገር ግን እንዳልሽው ያለመግባባት ወይም ደግሞ ያለመተዋወቅ ችግሮች አሉ መባሉ ትክክል ነው፡፡ ነገር ግን እሱ በኮሚሽኑ ሥራ ላይ ችግር አይሆንም፡፡ ምክንያቱም በእውነትም ስለማንግባባና ስለማንተዋወቅ ነው ችግሮች እየተፈጠሩ ያሉት፡፡ ስለዚህ ይህ ኮሚሽን የመጣውና ሥራውን እየሠራ ያለው ይህንን ችግር ለመቅረፍ ነው፡፡ በመሆኑም ያለመግባባቱና ያለመተዋወቁ ችግር በራሱ ችግር አይደለም፡፡

ኮሚሽኑ እንዲቋቋምና ሀገራዊ ምክክር ሊያመጣ የተፈለገበት ምክንያት ይኸውም በሚገባ ያለመተዋወቃችን የፈጠራቸውና የወለዳቸው ብዙ ችግሮች ስላሉ ነው፡፡

ላለመተዋወቃችንና በአግባቡ ላለመግባባታችን ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በእርግጥ እንድንግባባ እና እንድንተዋወቅ ተሠርቷል ወይ የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ይሁንና በአብዛኛውን ነገሮች የሚያተኩሩት ልዩነቱ ላይ ነው፡፡ መግባባት ወይም መተዋወቅ ማለት ሰዎች ከሰዎች ጋር አብረው ማዕድ ስለተጋሩና ስለተጫወቱ ተዋወቁ ወይም ተግባቡ ማለት አይደለም፡፡ መግባባት ከእዚህ አለፍ የሚል ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ መግባባትንና መተዋወቅን ለመፍጠር ቁጭ ብሎ መወያየትንና መመካከርን እንዲሁም ልብ ለልብ መነጋገርን ይጠይቃል፡፡ ቀደም ሲል ለመግባባት የሚያስችሉ መድረኮችም አልነበሩም፡፡ ይሁንና ሰዎች ወደመተዋወቁና መግባባቱ እንዲመጡ መሠራት ያለበት ሥራ ባለመሠራቱ ነው ይህ ውጤት ሊመጣ የቻለው፡፡ እንደሚባለው ማንም ቢሆን የሚያጭደው የዘራውን ነው፡፡ በመሆኑም አሁን የምናያቸው ያለመተዋወቅና ያለመግባባቶች ተዘርተው እየታጨዱ ነው ብሎ ማሰብ ይቻላል፡፡

ከዚህ አኳያ ሲታይ አንዱ ሀገራዊ ምክክሩን አስፈላጊ የሚያደርገው ነገር በኢትዮጵያ ውስጥ ይህ እውነት በመኖሩ ነው፡፡ በትክክል ልብ ለልብ የመተዋወቅና የመግባባት ችግር ስላለ ሰው ከሰው ጋር፤ አንዱ ብሔር ከሌላው ጋር ችግር ስላለበት ይህ ኮሚሽን እንዲወለድና ሥራዎችን እንዲሠራ ማድረግ ተችሏል፡፡

በዚህ ላይ መያዝ ያለበት አንዱ ቁም ነገር ምክክር የሚደረገው በተግባቡ ሰዎች መካከል አይደለም፡፡ በተግባቡ ሰዎች መካከል ምንም ምክክር አያስፈልግም፡፡ ምክክር የሚያስፈልገው ባልተግባቡና መሠረታዊ ልዩነቶች ባላቸው ሰዎች መካከል ነው፡፡ ይሁንና ሕዝቡ መግባባት የማይችለው ብዝሃነት ስላለው አይደለም፡፡ ብዝሃነት ላለመግባባት ምክንያት አይደለም፡፡ ብዝሃነት ተይዞ ግን ቁጭ ብሎ በመነጋገርና ልብ ለልብ በመደማመጥ እንዲሁም አንዱ የሌላው ጫማ ውስጥ ገብቶ ሁኔታዎችን በማየት ደረጃ ላይ መግባባት መፈጠር ነው እንጂ ብዝሃነት በራሱ ችግር አይሆንም፡፡ በተለያየ ቦታ ያለው የእርስ በእርስ አለመግባባት ምክክር ኮሚሽኑ ላይ የሚያሳድረው ምንም ዓይነት ጫና የለም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የፖለቲካ ስብራት የፈጠረው አለመግባባት በምክክር መድረኩ መጠገን የሚቻለው እንዴት ነው? ከታሪክ የተወረሱ ዕዳዎችስ የሚፈቱት በምን ዓይነት አካሔድ መሆን አለበት? እንደ ሀገር መግባባት ያልተደረሰባቸውን የትርክት መንስዔዎችስ በምክክር የሚፈቱት እንዴት ነው?**

**አቶ ጥበቡ፡-** እየታዩ ያሉ አለመግባባቶች እንዳሉ ሆነው እኛ አተኩረን የምንሠራው ብዙ ምክንያቶችና ብዙ መገለጫዎች ሊኖሩ ይችላል፡፡ እኛ ግን በአብዛኛው ዋና ትኩረታችን እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ አለመግባባቶች ላይ ነው፡፡ እነዚህ አለመግባባቶች በአጭር ጊዜ የተወለዱ ሳይሆኑ ለዘመናት የነበሩ ሲከማቹ ቆይተው ዛሬ የደረሱበት ደረጃ ላይ የደረሱ ናቸው፡፡

አለመግባባቶቹን የፈጠራቸው የፖለቲካ ስብራቶች ወይም ፖለቲካው አካባቢ ያሉ ቀውሶች የራሳቸው ሚና አላቸው፡፡ ነገር ግን ምናልባት ዋነኛ ምክንያት ናቸው ብሎ መውሰዱ ተገቢ ላይሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪ ከዚህ ጋር ተመጋጋቢ ሆኖ የሁሉም ድምር ውጤት ሊሆን ይችላልና፡፡ አሁንም ያለው ሆነ ቀደም ሲል የነበረው የፖለቲካ ሥርዓታችን የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

ሌላው ያነሳሽው ታሪኮቻችንን በተለያየ መንገድ የምንረዳበት ሁኔታ አለ፤ እንዳልሽውም መግባባት ላይ



ያልደረስንባቸው ትርክቶችም አሉ፡፡ ሆነ ተብለውም ለተለየ ዓላማ የሚሰራጩ ጉዳዮችም አሉ፤ እነዚህና መሰል ነገሮች ተደማምረው አሁን ለተፈጠረው ነገር አስተዋጽኦ አበርክተዋል ብለን እናምናለን፡፡

እንደ ሀገር ከምክክር ኮሚሽኑ ጋርም ተያይዞ ተመካክረን ልንሻገራቸው ከምንችላቸው ሃቆች መካከል የጠቀስሻቸው ነገሮች ናቸው፡፡ አንደኛ የፖለቲካ ሁኔታችን መሻሻልና መለወጥ አለበት፡፡ ሁለተኛ ደግሞ ታሪኮቻችን ላይ ለመግባባት ጥረት መደረግ አለበት፡፡ እንዲሁም በተዛባ ሁኔታ የሚፈጠሩ ትርክቶች የሆነ ቦታ ላይ ተግትተው መልክ መያዝ መቻል አለባቸው፡፡ ትናንት ነበሩ። ዛሬም አሉ፤ መፍትሔ ካልተገኘ ደግሞ ነገም ይቀጥላሉ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ሥራዎች የሚሠሩት ከእንደዚህ ዓይነት እሽክርክሪት ውስጥ ለመውጣት ነው፡፡

ከዚህ አኳያ ምናልባት በምክክር ኮሚሽኑ ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ እንደዓላማ ከተቀመጡ ነገሮች አንዱ እነዚህን የጠቀስሻቸውን ሁኔታዎች መቀየር ነው፡፡ አንዱ በምክክር ሒደቱ እንደርስበታለን ተብሎ የጠቀመጠው ዓላማ መተማመን የሰፈነበት እና አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት የመፍጠር ጉዳይ ነው፡፡

ሁለተኛው ደግሞ እንዳልሽው ሲንከባለሉ የመጡ ውስጣዊ ችግሮችን በውይይት ለመፍታት የሚያስችል የፖለቲካ ሥርዓት ማዳበር አንዱ ከምክክሩ የሚጠበቅ ጉዳይ ነው፡፡

ስለሆነም የኮሚሽኑ እንቅስቃሴ አሁናዊ ምልክቶችን ተከትሎ ሳይሆን መሠረታዊ ችግሮችን በመለየት ፈውስ ማምጣት ነው፡፡ ታክሞ በማገገምና በመፈወስ መካከል ልዩነት አለ፡፡ ስለዚህ እኛ በዋናነት የምናተኩረው የችግሩን ምንጭ በምክክር ሒደት በማግኘት ከዚያ አዙሪት ለመውጣት ሁነኛ መፍትሔ የመፈለግ አቅጣጫን ተከትለን በመሥራቱ ላይ ነው፡፡

በምክክሩ ሒደት ይህንን እንዴት እውን እናደርጋለን ለሚለው ጥያቄሽ እኛ የምናስበው በመጀመሪያ እነዚህ ጉዳዮች አጀንዳ ሆነው ይመጣሉ ብለን እንጠብቃለን፡፡ በእርግጥ ሊመጡም ላይመጡም ይችላሉ፡፡ አጀንዳ ሆነው ከመጡ ምክክር ይደረግባቸዋል፡፡ ስለዚህ በምክክር ሒደቱ ደግሞ እነዚህ ጉዳዮች ወደመግባባት ይመጣሉ ተብለው ይጠበቃሉ፡፡ ይህ ዝርዝር ነገሮችን የሚጠይቅ አንዳንዶቹ በአጭር ጊዜ፤ ሌሎቹ ደግሞ በተራዘመ ጊዜ ሊስተካከሉ የሚችሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ለረጅም ዓመታት ሲከማቹ የነበሩ ጉዳዮችን በአንድ ጀምበር የሚፈታበት ተዓምራዊ የሆነ ነገር ካልተፈጠረ በስተቀር ሊሆን ስለማይችል አንዳንዶቹ በአጭር ጊዜ ሊፈቱ ይችላሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ በረጅም ጊዜ ትግበራ ሊፈቱ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ የእኛ ተስፋ ጉዳዮቹ ላይ ምክክር በማድረግ ከእነዚህ አዙሪት ውስጥ የምንወጣበትን ነገር ሕዝቡ መክሮ እዚያ ደረጃ ላይ ይደርሳል የሚል እምነት አለኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኮሚሽኑ ከሕዝብና ከመንግሥት ጋር ተሰናስሎ የሚሠራው ሥራ ስኬታማ ይሆን ዘንድ ከሕዝብም ሆነ ከመንግሥት የሚጠበቀው ምንድን ነው?**

**አቶ ጥበቡ፡-** ሀገራዊ ምክክር እንደ ስሙ ሀገራዊ ነው፡፡ ስለዚህ ባለቤቱ ሕዝቡ ነው፡፡ ለሆነ አካል የተሰጠ አይደለም፡፡ ሀገራዊ ነው ካልን በውስጡ በርካታ ባለድርሻ አካላት አሉ ማለት ነው፤ ከዚህ ውስጥ አንዱና ዋነኛው ደግሞ ኅብረተሰቡ ነው፡፡ ሁለተኛ ደግሞ መንግሥት ነው፡፡ ቀጥሎ የተለያየ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሊሒቃን ናቸው፡፡ ከዚህ አኳያ ያሉት የተለያዩ አካላት ናቸው፡፡

ምክክሩ አለመግባባቶችንና ግጭቶችን ለመፍታት በባሕሪው ትንሽ ለየት የሚያደርገው ምክክር ሒደት ላይ ተሸናፊና አሸናፊ የሚባል ነገር አለመኖሩ ነው፡፡ ሁሉም አሸናፊ ሆኖ የሚመጣበት መድረክ ነው፡፡ አሸናፊ ሆነው የሚወጣው ነገር ደግሞ እውነት ነው፤ እውነት ደግሞ የሕዝብ ሐቅ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚያ አኳያ ሁሉም በእውነት ስለእውነት በጋራ ችግሩ ላይ ተነጋግሮ በጋራ መፍትሔ ላይ መድረስ ይቻላል ብለን እናምናለን፡፡ ስለዚህ ባለድርሻ አካላቱ እስካሁን ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ላደረጋቸው ጥረቶች ድጋፋቸው እጅግ የሚደነቅና የሚበረታታ ነው፡፡ ሕዝቡ እንደ ሕዝብ በሔድንባቸው ቦታዎች ላይ ሲያሳየን የነበረው ነገር እጅግ በጣም የሚደነቅ ነው፡፡ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሙያ ማኅበራትና ሌሎች የተለያዩ ተቋማት በሀገራዊ ምክክር ላይ ያላቸው ተስፋ እና የሚያደርጉት እገዛ በጣም የሚበረታታና መጠናከር ያለበት ነው፡፡ ይህም በቀጣይ ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንፈልጋለን፡፡

ከዚህ በመለስ ከኅብረተሰቡ አንዱ የሚጠበቀው ነገር ጫናዎች ቢኖሩበትም እነርሱን ተጋፍቶ በምክክር ሒደቱ ላይ ያለውን ተሳትፎ ሊያጠናክር ይገባል፡፡ የምክክር ሒደቱ ደግሞ ውጤት እንዲያመጣ የበኩሉን አስተዋጽኦ ሊያበርክት ይጠበቅበታል፡፡

ከዚያ በተጨማሪ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትም እስካሁን ሲያደርጉ የነበሩትን አስተዋፅኦ መቀጠል ይኖርባቸዋል፡፡ ከመንግሥትም አኳያ መወጣት የሚጠበቅበትና በአዋጁም የተቀመጠ ተግባራት አሉ፡፡ እስካሁን ባለው ሁኔታ ኮሚሽኑ ገለልተኛነቱንና ነፃነቱን በጠበቀ ሁኔታ እየተደረጉ ያሉ ድጋፎች በጣም የሚያበረታቱ ናቸው፡፡ ይህንኑ ድጋፍ አጠናክሮ መቀጠልና በምክክር ሒደቱ መጨረሻ ላይ ምናልባት የሚገኙ ምክረ ሃሳቦችን ተቀብሎ የመፈጸም ኃላፊነት የመንግሥት እንደመሆኑ መጠን ለዚህም ከወዲሁ መዘጋጀት አለበት፡፡

ምሁራኑና የፖለቲካው ማኅበረሰብ አካባቢም እንዲሁ እንደማንኛውም ባለድርሻ አካል በንቃት የመሳተፋቸው ነገር እንደተጠበቀ ሆኖ ተሳትፏቸው ጥናቶችን በማድረግ ሊሆን ይችላል፤ ምናልባትም በአካሄዳችን የታሪክ ችግሮች ሊኖሩ ስለሚችሉ እነዚያን በመንቀፍም ከኮሚሽኑ ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር ችግሮቹ እንዲፈቱ በማድረግ የበኩላቸውን ሚና መጫወትና ጉዳዩ ውጤት እንዲያመጣ አስተዋጽኦ ማበርከት አለባቸው ብለን እናስባለን፡፡

ከሚዲያም በተመሳሳይ ከጥበብ ማኅበረሰቡም ኅብረተሰቡ በጉዳዩ ላይ ግንዛቤ እንዲኖረው በማድረግና በተሻለ ንቃት በመሳተፍ ያላቸውን ክህሎት ተጠቅመው ደግሞ ተገቢውን ኃላፊነታቸውን ቢወጡ መልካም ነው ብለን እናስባለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኮሚሽኑ በተያዘው ዓመት የሚያካሒደው ውይይት ለሁሉም ችግር ቁልፍ ነው የሚሉ አካላት አሉ፤ ለዚህ ምላሽዎ ምንድን ነው?**

**አቶ ጥበቡ፡-** ጥሩ ጥያቄ ነው፡፡ እንደሚመስለኝ ኮሚሽኑ ለሁሉም ነገር ቁልፍ ነው ማለትም ሆነ ቁልፍ አይደለም ማለት ሁለት ጫፍ እና ጫፍ የወጡ ነገሮች ስለሚሆኑ ልክ ናቸው ብለን አናስብም፡፡ ለሁሉም ችግር መፍትሔ ነው ማለትም በሌላ በኩል ደግሞ ጭራሽ አያሳካም ማለትም ችግር አለበት፡፡ ስለዚህ እውነታውን የሚያሳዩት መሃል ላይ ያ ነገሮች ናቸው ብዬ አስባለሁ፡፡

እንግዲህ የሀገራችን ችግር ብዙ ነው፡፡ ዓይነቱም ምክንያቱም ብዙ ነው፡፡ ስለዚህ ኮሚሽኑን የእነዚህ ሁሉ ችግሮች መዳኛ መንገድ ነው ብሎ መውሰድ የራሱ ችግር አለበት፡፡ በዚያው ልክ ደግሞ ሀገራዊ ምክክሩ እንዳይሳካ የሚሠሩ ወገኖች አይሳካም ብለው ቢያወሩና ቢገምቱ ላይፈረድባቸው ይችላል፡፡ ምክንያቱም እንዳይሳካ መሥራት ሥራቸው ስለሆነ፡፡ በዚህ መሃከል ደግሞ ቀደም ሲል የተፈጠሩ ችግሮች ጥንካሬያቸውን በማየት ሊገምቱ የሚችሉ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

ስለዚህ ከዚህ አግባብ በኢትዮጵያ የሚካሄደው ሀገራዊ ምክክር የሚያተኩረው ደጋግሜ እንደገለጽኩት እጅግ መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የራሱ ውስንነት ሊኖረው ይችላል፡፡ ሁሉንም ጉዳዮች ስለማይመለከት ከዚህ አኳያ ገደብ ይኖረዋል ማለት ነው፡፡

ሌላው ለሁሉም ችግሮቻችን መፍትሔው ሀገራዊ ምክክር ብቻ ነው ማለት አይቻልም፤ ምክንያቱም አገልግሎት አሰጣጥንና አሠራርንም በማዘመን እና የፍትህ ሥርዓቱንና መሰል ጉዳዮችን በማሻሻል ደግሞ መመለስና መፈታት ያለባቸው ብዙ ችግሮች አሉ፡፡ ስለዚህ እዚህ ሀገር ያሉ ችግሮች በጣም የተከማቹና የተወሳሰቡ ዓይነታቸውም መንስዔያቸውም የተለያየ ስለሆነ እንደየሁኔታቸው መፍትሔ መስጠት ያስፈልጋል እንጂ ለሁሉም ነገር ሀገራዊ ምክክሩ መፍትሔ ነው ማለት አያስደፍርም፡፡

ነገር ግን አንድ ትልቁ ነገር እጅግ መሠረታዊ የሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ አተኩረን መሥራት ማለት የእርሱ ቅርንጫፎች የሆኑ ይከስማሉ እንደማለት ነው፡፡ ምክንያቱም የችግሩ ምንጭ ስለተመታ ሌላው ችግር በራሳቸው ጊዜ ሊፈቱ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ከዚህ አግባብ ትልልቆቹ አጀንዳዎች ላይ መግባባት መቻሉ ለትንንሾቹ ጉዳዮች መፍትሔ ይሆናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ትልልቆቹ አጀንዳዎቻችን ላይ መግባባት ላይ ከደርስን ሌሎቹም የሚፈቱ ስለሚሆን መንግሥትም የተረጋጋ ሥራ መሥራት የሚያስችለው ሁኔታ ከመፈጠሩም በተጨማሪ ሕዝቡም የተረጋጋ ኑሮ እንዲመራ ምክንያት ይሆነዋል የሚል እምነት አለን፡፡ ከዚህ አኳያ ምክክሩ የሁሉም ችግሮቻችን መፍትሔ ባይሆንም ለዋና ዋና ችግሮቻችን ግን መፍትሔ ይሆናል ብለን እናምናለን፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ሰፊ ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡**

**አቶ ጥበቡ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## የኢሬቻ በዓል አድማቂ ባሕላዊ አልባሳት

**ወርቅነሽ ደምሰው**



በኦሮሞ ብሔር ዘንድ በየአመቱ በመስከረም ወር የሚከበረው የኢሬቻ በዓል በደማቅ ሥነሥርዓት ይከበራል:: በዓሉ የአደባባይ በዓል እንደመሆኑ መጠን በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች ይሳተፉበታል:: በዓሉ የኦሮሞን ሕዝብ የተለያዩ አካባቢዎችን የሚገልጹ ባሕላዊ አልባሳት በብዛት ይንጸባረቁበታል:: እነዚህ በዘመናዊ መልኩ ባማረ ዲዛይን የተሠሩ ባሕላዊ አልባሳት ለበዓሉ ልዩ ድባብን ይፈጥራሉ:: ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ባሕላዊ ይዘታቸውን ሳይለቁ የተሠሩ የፋሽን አልባሳትን ለብሶ መድመቅ እየተለመደ መጥቷል::

ከሕፃናት እስከ አዛውንት ያሉ የበዓሉ ተሳታፊዎች በተናጠል እና በቡድን ሆነው የሚለበሷቸው ባሕላዊ አልባሳት የሰውን ቀልብ በእጅጉ የሚስቡ ውብና ማራኪ ከመሆናቸው ባሻገር፣ በየዓመቱ እየዘመኑ በተለየ ውበት ተሠርተው እየቀረቡም ናቸው:: እነዚህ አልባሳት የኦሮሞን ሕዝብን ቱባ ባሕል እየፈለፈሉ አውጥቶ በማሳየት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው የፋሽን ዘርፉ ባለሙያዎችም ይናገራሉ::

በኢሬቻ በዓል የኦሮሚያ የተለያዩ አካባቢዎችን ባሕል የሚያንጸባርቁ አልባሳት መለበሳቸው ለበዓሉ ውበት ሆነው ለየት ያለ ድባብ እንደሚፈጥሩ የምትናገረው የኦሮሞ ባህላዊ አልባሳት ዲዛይን በማድረግ የምትታወቀው ዲዛይነር ሌሊሴ ግርማ፣ በዓሉ አልባሳት ባሕላዊ ይዘታቸውን ሳይለቁ በዲዛይን ተሠርተው የሚለሱበት መሆኑን ትጠቁማለች::

በበዓሉ በቤት የሚቀር ሰው የሌለ እስከሚመስል ድረስ በርካታ ሰዎች የሚሳተፉበት ስለሆነ በዕለቱ የሚታዩት አልባሳት ይህም አለ እንዴ? ይህ ደግሞ የየት አካባቢ ልብስ ነው የሚያስብሉ ስትል ገልጻ፣ እንኳን ለተመልካቹ የበዓሉም ታዳሚዎችን ጭምር በማስደመም እርስ በርስ፤ ባሕልን ከባሕል ለማስተዋወቅ ያላቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው ትላለች::

ዲዛይነር ሌሊሴ እንደምትለው፤ ለኢሬቻ በዓል የሚለበሱ አልባሳት በተለየ መልኩ የሚሠሩ ናቸው:: የኦሮሞ ባሕላዊ አልባሳት ሲሠሩ የሆነ አካባቢን የሚገልጹ እና አባገዳ በመባል የሚታወቀው አልባሳት ጥለት ሊኖርባቸው የግድ ነው:: ኦሮሞ ሕዝብ ባሕልን ሊገልጹና ሊያንጸባርቁም የሚችሉ መሆን አለባቸው:: የኦሮሚያ ሰንደቅ ዓላማ ቀለማት ጨምሮ ከረዩ፣ ጉጂ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ወለጋ፣ ሸዋ እና የመሳሰሉት አካባቢዎች አልባሳት በጥለቱ እና በአሰፋፋቸው የሚገልጹ መሆን አለባቸው::

አልባሳቱ በጥለታቸውና በአስፋፋቸው የየት አካባቢ አልባሳት እንደሆኑ ይታወቃሉ የምትለው ዲዛይነሯ፤ ጥለቱ ላይ የትኛውንም ዓይነት ቀለም ተጠቅሞ ሁለት አካባቢዎች ወይም የተለያዩ አካባቢዎች እንዲገልጹ አድርጎ መሥራት ወይም የሆነ ጥለትን አስገብቶ አዲስ ዲዛይን በመፍጠር በተለይ መልኩ ፋሽን የሆኑ ልብሶችን መሥራት ይቻላል ትላለች::

በኢሬቻ በዓል በብዛት የሚለበሱት አባገዳ በመባል የሚታወቀው ጥለት ያላቸው አልባሳት ሲሆኑ፣ እነዚህ አልባሳት በአብዛኛው ለባሽ ዘንድ ተመራጭ መሆናቸውንም ዲዛይነሯ ትገልጻለች:: የአንድን አካባቢ ባሕል ብቻ ከሚያንጻባርቁ አልባሳት ይልቅ አባገዳ ጥለት ያላቸው አልባሳት አካባቢን ስለማይለዩ በብዛት ተመራጭ እንደሆኑም ትናገራለች:: የወለጋ፣ የሸዋ፣ የባሌ፣ አርሲ፣ ጉጂ እና የከሚሴ አካባቢ አልባሳትም እንደዚሁ በብዛት እንደሚለበሱ ጠቅሳ፣ እነዚህን አልባሳት የሚያሠሩ ተጠቃሚዎች እንዳሉም ትናገራለች::

አባገዳ ያለባቸው አልባሳት ሁሉንም በማከለ የሚሠሩ ሲሆን፣ ለሴቶች የሚሆኑ አልባሳት ሲሠሩ ‹ጮጮ›፣‹ቀቤ›፣‹ሲንቄ›፣‹ጨሌእናሌሌላ› የሚባሉት ማካተት አለባቸው:: ለምሳሌ የሴቶች ልብስ ሲሠራ ጨሌ ማስገባት ካስፈለገ የየትኛው አካባቢ ሊገለጽ እንደተፈለገ ከተለየ በኋላ ያንን አካባቢ እንዲገልጽ ተደርጎ ጨሌው ልብሱ ላይ እንዲገባ ይደረጋል ትላለች::

የወንዶች አልባሳትም እንዲሁ ‹ከለቻ›፣‹ቦኩ›፣ ‹ጋቸና› እና ‹ሊቦ› የሚባሉ ከልብሱ ጋር ሊሄዱ የሚችሉ ነገሮችን በመጠቀም እንደሚዘጋጁ ጠቅሳ፣ እነዚህ ጀግንነትን የሚያሳዩ በመሆናቸው በልብሶቹ ላይ እንደሚካተቱ ትገልጻለች:: ለምሳሌ ‹ሊቦን› የተሰኘውን ከወለጋ አካባቢ ልብሶች ጋር በመጠቀም መሥራት ሲቻል፤ ‹ጋቸና› የሚባለውን ደግሞ ከየትኛው አካባቢ ልብስ ጋር የሚሄድ ስለሆነ ከሁሉም አካባቢ ልብሶች ጋር መሥራት ይቻላል ስትል ታብራራለች:: እነዚህ ዓይነት አልባሳት ሲሠሩ ጀግንነትን የሚያሳዩ፣ ፈረስ ላይ የሚያስወጡ ዓይነት ዲዛይን ያላቸው ቢሆኑ ተመራጭ ነው ትላለች::

ለበዓሉ የሚያስፈልጉትን እንደ ‹ቦኩ›፣‹ጮጮ› እና ሲንቄ ያሉትን ለማዘጋጀት ጊዜ እንደሚጠይቅ ጠቅሳ፣ ከእነዚህ ጋር አብረው ሊሄዱ የሚችሉ አልባሳት ዲዛይን አድርጎ መሥራት እንደሚጠበቅ ነው የተናገረችው::

አባገዳዎች የሚለበሷቸው ራሳቸውን የቻሉ ጋቢዎች እንዳሉም ጠቁማለች:: አልባሳቱ ሱሪ በቲሸርት ከጋቢ ጋር፤ ከ‹ቦኩ› ጋር እንዲሁም ‹ከለቻ› የሚባል ግንባር ላይ የሚደርግ የአባገዳ ልብስ የሚያንጸባርቁ መሆን እንዳለባቸው ታብራራለች:: አባገዳ ሁሉንም አካባቢ ወክሎ የሚደረገ ስለሆነ አባገዳ ያለበት ልብስ አንድን አካባቢ ብቻ ለይቶ የሚያሳይ ሳይሆን ሁሉንም የኦሮሚያ አካባቢዎች የሚገልጽ ነው ማለት እንደሚቻል ታብራራለች::

አልባሳቱ ዘመናዊ ተደርገው ሲሠሩ ባሕላዊነታቸውን እንደጠበቁ ተደርገው መሠራት አለባቸው የምትለው ሌሊሴ፤ የኦሮሞ ሕዝብ በተለይ በኢሬቻ ላይ የሚያስቀምጣቸው የራሱ ባሕላዊ ትውፊቶች እንዳለው ትናገራለች:: ለምሳሌ በአባገዳ ሥርዓት ሴቶች መገላለጥም ሆነ አጭር ቀሚስ መልበስ የለባቸውም:: ኢሬቻ በዓል ለማክበር የሚወጣው ነጭ ልብስ ተለብሶ፣ ሁሉንም የኦሮሚያ አካባቢዎች ተከቶ በመሆኑ እነዚህን ሥርዓቶች ያሚሉ ሥራዎችን መሥራት የግድ ይላል:: ለባሹም ፋሽን የሚለብስም ቢሆንም ባሕላዊ ሥርዓቱን የጠበቀ ልብስ በመልበስ አምሮበትና ተውቦ የመገኘት ኃላፊነት እንዳለበት አስገንዝባለች::

በበዓሉ የተለበሱ አልባሳት ከበዓሉ በኋላ በተለያዩ ማኅበራዊ ሚዲያዎች በፌስቡክ፣ በኢንስታግራም፣ በቲክ ቶክ እና የመሳሰሉት ድረ ገጾች ላይ ስለሚለቀቁ የማን ሥራ እንደሆነ ጭምር የሚታወቅበትና ሕዝቡም አስተያየት የሚሰጥበት ነው የምትለው ሌሊሴ፤ ከዚህ አንጻር የምትሠራቸው ሥራዎች ባሕላዊነታቸውን ሳይለቁ እንደሚሠሩ፣ ለደንበኞቿም ይህንኑ ምክረሀሳብ እንደምትለግስ ትናገራለች::

ዲዛይነሯ እንደምትለው፤ ለበዓሉ ሁሉም በሚባል ደረጃ አምሮና ደምቆ ለመታየት የሚያስችለውን ልብስ ይሸምታል:: በተለይ አሁን ላይ ፋሽን ልብሶች የሚፈለጉት ለበዓሉ ብቻ ሳይሆን ከበዓሉ በኋላም በማንኛውም ቦታ ላይ ሊለበሱ የሚችሉ በመሆናቸው ነው:: ባሕሉን የሚያንጸባርቁ ለወንድም ለሴትም የሚሆኑ ቀለል ያሉ ቀሚሶች፣ ቲሸርቶች እና የመሳሰሉት ሥራዎች ይፈልጋሉ:: እነዚህ አልባሳት የውጭ ሀገር ዜጎችን ሳይቀር የሚማርኩና የሚስቡ ስለሆኑ ሌሎችም ወደውት እንዲለብሱ ያደርጋል ትላለች::

አንድ ልብስ ለመሥራት የሚፈጀውን ጊዜና ቁሳቁስ ታሳቢ ያደረገ ዋጋ ለልብሶች እንደሚወጣላቸው የምትናገረው ዲዛይነሯ፤ ይህም ሆኖ ግን በተለይ በኢሬቻ በዓል ለባሹ የፈለገውን በአቅሙ ሸምቶ መልበስ እንዲችል ሁሉንም ሊለብስ በሚችል መልኩ የሚዘጋጁ ልብሶች መኖራቸውን ትናገራለች::

በሌላ በኩል ደግሞ የመግዛት አቅም የሌላቸው የሚፈልጉትን ዓይነት ባሕላዊ ልብስ ተከራይተው መልበስ የሚያስችለው አማራጮች እንዳሉም ትጠቁማለች:: በተለይ የተለያዩ አካባቢዎችን የሚገልጹ አልባሳት በኪራይ ተዘጋጅተው ስለሚቀርቡ ተጠቃሚዎች ተከራይተው መልበስ እንደሚችሉ ጠቅሳ፤ የኪራይ ዋጋቸውም እንደቦታው ቢለያይም ከ1ሺ እስከ 3ሺ ብር ድረስ እንደሚገኝ ትገልጻለች::

የኢሬቻ በዓል በየዓመቱ አዳዲስ ነገሮች የሚታዩበት የበዓሉ ተሳታፊዎች በየጊዜው እየጨመሩ የሚመጡ እንደመሆኑ መጠን ከዓምና አንጻር ዘንድሮ በርካታ ልብስ ለማሠራት ሆነ ለመሸመት የሚፈልጉ ሰዎች የታዩበት እንደሆነ ዲዛይነር ሌሊሴ ትናገራለች ፡

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ‹‹ፋራ›› ሲሠለጥን.....

**ዋስልኝ አየለ**

ምንም እንኳን የዕለት ከዕለት ገጠመኝ ቢሆንም፤ ሙሉ የታክሲውን ሰው ያስገረመ አንድ ገጠመኝ መነሻ ላድርግ:: ከቦሌ አራብሳ ወደ መገናኛ ልሄድ ነው:: ታክሲው ሊሞላ የኋላ ወንበር ብቻ ይቀራል:: ገብቼ የኋላው ወንበር በቀኝ በኩል ባለው ጫፍ ላይ ተቀመጥኩ:: ወዲያውኑ አንዲት ወጣት ስልክ እያወራች ገባች:: አለባበሷ በተለምዶ የአራዳ አለባበስ የሚባለው የተቀዳደደ ሱሪ ነው:: አነጋገሯም በተለምዶ የአራዳ አነጋገር በሚባለው ቅላጼ እና በተለምዶ የአራዳ በሚባሉት ቃላት ነው::

ታክሲው ሞልቶ ጉዞ ተጀመረ:: ልጅቷ በጣም እየጮኸች፣ ጣሪያ የሚሰነጥቅ ሳቅ እየሳቀች ታወራለች:: የምታወራው ወሬ ደግሞ ከሰው መሃል ሆኖ ለማውራት የሚያስገድድ አይደለም:: ስለአንዲት የወለደች ጓደኛቸው ነው በስልክ ከምታወራት ጓደኛዋ ጋር የሚያወሩት:: አጠገቧ ሰው ያለ አይመስላትም::

ሌሎች ሰዎች አጫጭር የሆኑ የመልዕክት ስልኮችን እንኳን ማውራት አልቻሉም፤ በጣም ትጮሃለች:: ብዙ ሰዎች እየዞሩ ያዩዋታል፤ የብሽቀት መሆኑ ፊታቸው ላይ ያስታውቃል:: አንዳንዶቹም ከጎናቸው ካለ ሰው ጋር ትዝብታቸውን ይለዋወጣሉ:: በዚያ በተዘጋጋ መንገድ ከቦሌ አራብሳ እስከ መገናኛ እንደዚያው እንደጮኸች ሳትጨርስ ከታክሲው ወርደን በየፊናችን ሄድን::

ታዲያ ይሄ ምኑ ይገርማል? ይባል ይሆናል::

የሚገርመውማ አራዳ፣ የሠለጠነች፣ የዘመነች መስሏት የመሃይም ሥራ መሥራቷ ነው:: በእሷ ቤት መብቷን የምትጠቀም፣ ነፃነቷን የምትጠቀም የጨሰች አራዳ መሆኗ ነው:: ሰዎችን መረበሽና ምቾት መንሳት ግን ኋላቀርነት ነው:: አለባበሳቸውን ብቻ የኮረጀችው የፈረንጆች ባህል ግን ሰዎችን መረበሽን አይፈቅድም:: የሠለጠኑ የሚባሉት ሀገራት ትልቅ የሥልጣኔ መገለጫቸው የሰዎችን መብት ማክበር ነው:: መብት በመብት ይገደባል:: እሷ የመጮህ መብት ቢኖራት አጠገቧ ያሉ ሰዎች ያለመረበሽ መብት አላቸው:: እያወራሁ ያለሁት ስለአንዲት ግለሰብ ሳይሆን በዚች ልጅ ወካይነት የብዙ ሰዎችን ኋላቀር የሆነ አጉል መሠልጠን ነው::

የሠለጠኑ ናቸው የሚባሉ ብዙ ሀገራት ሰዎች የሚበዙበት ቦታ (public Space ይሉታል) ላይ ስልክ ማውራት ይከለክላሉ:: በሚገርም ሁኔታ ምግብ ቤት ውስጥ እንኳን የሚከለከልበት ሁኔታ አለ:: ትራንስፖርት ውስጥማ መደበኛ ሕግ ነው ማለት ይቻላል:: በኢትዮጵያ ግን በስብሰባ ቦታ እንኳን ማስቀረት አልተቻለም:: በሠለጠኑት ሀገራት የጋራ በሆኑ ነገሮች (ለምሳሌ ታክሲ) የግል ፍላጎትን ብቻ ማስተናገድ በሕግ ብቻ ሳይሆን በሞራልም ነውር ነው:: የአንድ ሰው ሥልጡንነት የሚለካው ለሌሎች በማሰቡ ነው::

በእኛ ሀገር ግን የሚታየው በተቃራኒው ነው:: ‹‹ማንንም አትስማ! ለሰዎች አትጨነቅ! ራስህን ብቻ አዳምጥ!...›› የሚሉ ነገሮች እንደ መሠልጠን ነው የሚቆጠሩት:: ለሰዎች አለማሰብ፣ ማንንም አለመስማት ኋላቀርነት እንጂ መሠልጠን ሊሆን አይችልም::

የተኮረጀ ነገር ችግሩ ይኸው ነው:: ነፃነትንና መብት መጠቀምን ስንኮርጅ አጠቃቀሙን ግን አልኮረጅንም:: ሰዎችን መረበሽ በምንም መንገድ ነፃነትና መሠልጠን ሊሆን አይችልም፤ ይሉኝታ ቢስነት ነው:: ደግሞ እኮ እነዚህ አራዳ ነን የሚሉ ሰዎች ሌላ ሰው ቢረብሻቸው በይሉኝታ እንኳን የሚያልፉ አይደሉም:: እነርሱ ሲረብሹ ግን መብታቸው ነው!

በዚህ አጋጣሚ እስኪ ስለአራዳነትም እንታዘብ:: አራዳ የሚለው ቃል መደበኛ ቃል አይደለም:: አገላለጹ የተጀመረው ከጣሊያን የአምስት ዓመቱ ቆይታ በኋላ ነው ይባላል:: አራዳ ማለት ያለፈውንም የዘመኑንም እውቀት የገባው፣ የዘመነ፣ የተማረ ማለት ነው:: በኢትዮጵያ አራዳ ተብለው የሚጠሩ ሰዎች የተፈጠሩት የጣሊያን እና ሌሎች ነጭ ዜጎች በኢትዮጵያ በተለይም በአዲስ አበባ ውስጥ መምጣታቸውን ተከትሎ ነው:: አራዳ የሚባሉትም፤ የፈረንጅ ቋንቋ የሚችሉና ስለዓለም ብዙ አንብበው ሰምተውና አይተው የዓለምን ሁኔታ ለኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው የሚያስተነትኑ እና በአኗኗራቸውም ሠልጠን ያሉ የከተማ ሰዎች ናቸው::

በሂደት ግን አራዳ የሚለው ቃል ሌላ ትርጉም እየያዘ መጣ:: በየከተሞች ለሚገኙ ተራቢዎች፣ አሸሙረኞች ተላካፊዎች፣ አጭበርባሪዎች፣ አታላዮች፣ እና ሱሰኞችን ለመግለጽ የሚያገለግል ቃል ሆነ:: ይሄኛውን ትርጉሙን ያዛመቱት አዝማሪዎች ናቸው ይባላል:: እንዲያውም ሰሞኑን አንድ ትንሽዬ አዝማሪ ልጅ መሰንቆ ይዞ ስለአራዳነት ሲዘፍን በማኅበራዊ ገጾች ሲዘዋወር ነበር::

የመጀመሪያውን የአራዳነት ትርጉም እንውሰድ:: የዘመነ፣ የተማረ፣ የጥንቱንም የአሁኑንም ዕውቀት ያለው፣ ለሥልጣኔ ፈጣን የሆነ ማለት ነው:: እነዚህ ነገሮች ደግሞ ከምዕራባውያን የሚወሰዱ ናቸው:: በከተሞች አካባቢ በስፋት የታየበት ምክንያትም የውጭውን ዓለም የማየት ዕድል ያለው በስፋት ከተማ ውስጥ ስለሆነ ነው:: አራዳነት ግን የግድ የፈረንጆችን መኮረጅ መሆን አልነበረበትም:: ብዙዎቻችን ግን ቢያንስ የፈረንጆችን እንኳን በትክክል መኮረጅ አልቻልንም::

ብዙ ወጣቶች የንግግር ቅላጼዎቻቸውን በእንግሊዝኛ አፋቸውን የፈቱ ለማስመሰል ሲፍጨረጨሩ፣ በአለባበሳቸውና ፀጉር አቆራረጣቸው ምዕራባውያንን ለመምሰል ሲታገሉ፣ በእጅ የሚበላ ምግብ በሹካ ወይም በማንኪያ ለመብላት ሲደክሙ.... በዚህ ሁሉ ጥረት ውስጥ ግን የአዕምሮ መሠልጠናቸውን አይኮርጁም::

‹‹ፋራ ሲሠለጥን›› የሚባል የተለመደ አገላለጽ አለ:: አራዳ ማለት ከላይ የገለጽነው ከሆነ ፋራ ማለት ደግሞ የዚያ ተቃራኒ ማለት ነው:: ነባራዊ ሁኔታዎችን የማያገናዝብ፣ ነገሮች የማይገቡት፣ ብልህና አስተዋይ ያልሆነ ማለት ነው:: እንዲህ ዓይነት ሰዎችን ነው የአራዳ ልጆች ‹‹ፋራ ሲሠለጥን...›› የሚሏቸው:: ምክንያቱም እነዚህ ፋራ የሚባሉ ሰዎች የሠለጠኑ መስሏቸው የሚያደርጉት ነገር ሌሎችን የሚረብሽና ምቾት የሚነሳ ነው:: ለምሳሌ፤ ትራንስፖርት ውስጥ የጆሮ ማዳመጫ (ኤርፎን) ከመጠቀም ይልቅ ስልካቸውን ድምጹን ከፍ አድርገው ሙዚቃ ወይም ሌላ ነገር ይከፍታሉ:: አጠገባቸው ያለ ሰው እየተረበሸ ነው ማለት ነው::

የዚህ ትዝብት መነሻ የሆነኝ ስልክ በጣም እየጮኹ ማውራት የብዙዎች መገለጫ እየሆነ ነው:: ስልክ አይወራ ማለቴ አይደለም:: እንደ ጉዳዩ ሁኔታ ከታክሲ እስከሚወርዱ የማያደርስ ሊኖር ይችላል፤ የቀጠሮ መልዕክት ሊሆን ይችላል:: እነዚህ ደግሞ ቢበዛ በአንድ እና በሁለት ደቂቃ ውስጥ የሚያልቁ ናቸው:: አንዳንዶቹ ግን መቼም ቢሆን ሊወራ የሚችል የቤት ውስጥ ገመና ነው ታክሲ ውስጥ የሚያወሩት:: ሌላው ሰው የግድ የእነርሱን ገመና መስማት አለበት?

እነዚህ ሰዎች ታክሲ ውስጥ ‹‹አትጨኹ›› ቢባሉ ምን እንደሚሉ ግልጽ ነው:: ‹‹መብቴ ነው!›› ነው:: ‹‹በራሴ ስልክ፣ በራሴ ካርድ ምን አገባህ?›› የሚል ቁጣ እና ስድብም ይኖረዋል:: ራሳቸውን እንደ መብትና ነፃነት ተጠቃሚ በማየት የተናገራቸውን ሰው ምናልባትም እንደ ኋላቀር ሊያዩት ይችላሉ:: መሠልጠን ማለት ግን የሌሎችንም ነፃነት መጠበቅ ነው:: መሠልጠን ማለት ሰዋዊ ይሉኝታ ሲኖረው ነው:: መሠልጠን ማለት የግድ እስከሚከለከል መጠበቅ ሳይሆን ልክ ያልሆኑ ነገሮችን የሚያውቅ ማለት ነው::

በብዙ ነገሮች ላይ መብት ብርቅ የሆነብን ይመስላል:: ልክ ያልሆነ ነገር ያደረገ ሰው፤ በማድረጉ ሲቆጡት ‹‹መብቴ ነው!›› ይላል:: መብት ተፈጻሚ የሚሆነው እኮ ሌሎችን በማይረብሽና በማይጎዳ መንገድ ሲሆን ነው:: መብት ተፈጻሚ የሚሆነው ሕግና ደንቦችን የማይተላለፍ ከሆነ ነው:: ከዚያ ውጭ አንድ ሰው ማድረግ ያስፈለገውን ሁሉ ሊያደርግ አይችልም፤ ምክንያቱም መብት በመብት ይገደባል::

ጎሊና ለሰው ልጅ የተሰጠ ለሌሎች ማሰብ ነው:: በሕግ በመከልከል ሳይሆን በማሰብ ማድረግና አለማድረግ ማለት ነው:: ስለዚህ ከሕግ በላይ ለኅሊናም ተገዢ በመሆን ሌሎችን የሚረብሹ ነገሮችን አናድርግ!

# በአንድ ዓመት ውስጥ አምስት ቢሊዮን ዶላር ያጣው የጋናው ብሔራዊ ባንክ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**




በአሁኑ ወቅት ጋና ከዚህ ቀደም አይታው የማታውቀው የገንዘብ ቀውስ አጋጥሟታል። ተቃዋሚዎች በመዲናዋ አክራ ጎዳናዎች ላይ በመውጣት የጋና ባንክ ገዢ እና ምክትሎቻቸው ሥራቸውን እንዲለቁ ጠይቀዋል።

የብሔራዊ ባንኩ ገዢና ምክትሎቻቸው ባለፈው ዓመት 60 ቢሊዮን ሲዲ (የጋና መገበያያ ገንዘብ) ወይም አምስት ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ዶላር አጥፍተዋል በሚል ነው ከኃላፊነታቸው እንዲለቁ መጠየቃቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

ባንኩ ለመንግሥት ብድር ለመስጠት ሲል በሕገወጥ መንገድ ገንዘብ አሳትሟል ሲሉ ተቃዋሚዎች ይወቅሱታል። ይህም ሁኔታ የሀገሪቷ መገበያያ ገንዘብ አቅም እንዲያሽቆለቁል እና የዋጋ ግሽበት እንዲፈጠር አድርጓል ይላሉ።

ሌላኛው ባንኩ የሚተችበት ለሀገርና ለውጭ ጉዞ ከ762 ሺህ ዶላር በላይ ወጪ አድርጓል፤ እንዲሁም አዲስ ሕንጻ ለመገንባት 250 ሚሊዮን ዶላር ወጪ ማድረጉን በመጥቀስ ነው። ተቃዋሚዎች ባንኩ ያወጣቸው ወጪዎች በሙሉ በባንኩ የውስጥ ኦዲት ውስጥ ተመዝግበዋል ይላሉ።

"ይህንን የመሰለ ነገር በታሪካችን አይተን አናውቅም። የጋና ባንክ ከዚህ ኪሳራ እንዲያገግም ከተፈለገ ከ45 ዓመታት በላይ ይፈጅባቸዋል" ሲሉ የጋና ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት ፕሮፌሰር ጎድፍሬድ ቦክፒን ይናገራሉ።

ባንኩ በበኩሉ ኪሳራው የተከሰተው ተለዋዋጭ በሆነ የምንዛሪ ሥርዓትና የመንግሥት ተቋማት የማይከፈል ብድር በመውሰዳቸው ነው።

በተጨማሪም የጋና መንግሥት 700 ሚሊዮን ዶላር ተበድሮ ሙሉ በሙሉ ባለመመለሱ ለችግሩ መባባስ አስተዋጽኦ አድርጓል ይላሉ።

የባንኩ ገዢዎች በተከተሉት የገንዘብ ፖሊሲ በሀገሪቱ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት እንዲመጣ በማድረጋቸው እየተወቀሱ ነው።

"ለመንግሥት በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ሲያሳትሙ ምን አይነት ውጤት እንደሚያስከትል አያውቁም ነበር?" ሲሉ የሕግ ባለሙያው ማርቲን ኬፐቡን ይጠይቃሉ።

ባለፈው ዓመት በጋና የዋጋ ግሽበቱ 54 በመቶ ሆኖም ተመዝግቧል። ይህ በሀገሪቱ ከፍተኛ አሃዝ ሆኖ የተመዘገበ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅትም ከ40 በመቶ በላይ ነው።

ሀገሪቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ የመበደር አቅሟም እንደወረደ የብድር ተቋማት ደረጃዋን ዝቅ አድርገዋል። የጋና አጠቃላይ ዕዳ ሲታይ ባለፈው ዓመት መስከረም ወር ላይ ወደ 55 ቢሊዮን ዶላር ከፍ ማለቱ ታይቷል። ይህም ማለት መንግሥት ዕዳውን ለመክፈል ከገቢው 70 በመቶ በላይ ያስፈልገው ነበር።

ጋና በተያዘላት ወቅትም ዕዳዋን መክፈል አልቻለችም። የጋና መንግሥት የብድር ሽግሽግን አስመልክቶ ከአበዳሪዎች ጋር እንደገና መደራደር፣ በመንግሥት ብድር ላይ ዝቅተኛ የወለድ መጠንን የማስቀመጥ ሃሳብ አቅርቧል።

በተጨማሪም በሕዝብ ፋይናንስ ላይ ያለውን ጫና ለማቃለል ረዘም ያለ የብድር የመክፈያ ጊዜን የያዘ የድርድር ሃሳብ አቅርቧል። ሆኖም አንዳንድ አበዳሪዎች በዚህ የመንግሥት ፕሮግራም ላይ ለመሳተፍ ፈቃደኛ አልሆኑም።

ባለፈው ዓመት መጨረሻ ላይ መንግሥት የአይኤምኤፍን መስፈርት ለማሟላት በቂ ገንዘብ እንደሌለው እና በዚህም ምክንያት ከባንኩ የተበደረውን 700 ሚሊዮን ዶላር ግማሹን እንደማይከፍል በመግለጽ የጋና ባንክ መግለጫ አውጥቷል።

መንግሥት ከባንኩ የተበደረው ገንዘብ ዕዳውን ለማሸጋሸግ እንደሚውልና ለባንኩ ምንም አይነት ወለድም እንደማይከፍል ተናግሯል።

የሀገሪቱ ባንክ በፖሊሲ ደረጃ ለመንግሥት የመጨረሻው አማራጭ አበዳሪ ቢሆንም ፕሬዚዳንት ናና አኩፎ አዶ የሚመሩት መንግሥት ከዚህ ተቃርኗል ይላሉ። መንግሥት ባንኩን እንደበዘበዘና የባንኩን ሕግጋት እንደጣሰ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

"የጋና ባንክ ሕግ በጣም ግልጽ ነው። ገንዘብን ማተም ወይም ለመንግሥት የገንዘብ ድጋፍ የሚደረገው ከባንኩ ገቢ በአምስት በመቶ ብቻ የተገደበ ነው። ይህም ማለት በመርህ ደረጃ መንግሥትን መደገፍ ወንጀል ባይሆንም፣ ነገር ግን ከአምስት በመቶ በላይ መሄድ አይቻልም" ይላሉ ፕሮፌሰር ቦክፒን።

መንግሥት ከአምስት በመቶ ገደብ ካለፈ የባንኩ ኃላፊዎች ለፓርላማ ሪፖርት እንዲያቀርቡ ሕጉ ደንግጓል። ይህንን ሪፖርት አለማድረግ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከሁለት ዓመት የማይበልጥ እስራት ሊያስቀጣ ይችላል። ይህ ማለት የጋና ባንክ ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ከስሯል ማለት አይደለም።

ማዕከላዊ ባንኩ የተቋቋመው እንደ ንግድ ባንኮች ትርፍ ለማግኘት አይደለም። ስለዚህ ኪሳራው በመደበኛ ሥራው ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር አይገባም።

ባንኩ እንደ መጨረሻ አበዳሪነቱም የራሱን ገንዘብም ማምጣት ይችላል። ነገር ግን የማዕከላዊ ባንኩ ኪሳራ በሀገሪቱ ላይ ቀውሶችን እንደሚያስከትል ባለሙያዎች ይናገራሉ።

ምንም እንኳን በዓለም ዙሪያ ያሉ ሌሎች ማዕከላዊ ባንኮች ተመሳሳይ ፈተናዎች ቢያጋጥማቸውም የጋናን ልዩ የሚያደርገው ግን ሀገሪቷ ያላት የምጣኔ ሀብት ከጠፋው ገንዘብ ጋር ሲነጻጸር ነው።

ለምሳሌ በዩናይትድ ኪንግደም የእንግሊዝ ማዕከላዊ ባንክ በሚቀጥሉት ዓመታት ውስጥ 180 ቢሊዮን ዶላር ገደማ የሚያጣ ሲሆን፤ የዩናይትድ ኪንግደም ምጣኔ ሀብት በትሪሊዮን ዶላር የሚቆጠር ነው።

የጋና ባንክ የደረሰበትን ኪሳራ ከሌሎች ሀገራት ጋር ማወዳደር ተገቢ እንዳልሆነም የማኅበራዊ ፈጠራ ባለሙያ እና ደራሲው ብራይት ሲሞንስ ይናገራሉ።

አብዛኛው ብልሽት የተፈጠረው ባንኩ የመንግሥት ልቅ የፊሲካል ፖሊሲን በመቀበሉ እንደሆነም ያስረዳሉ። በሌላ አነጋገር ባንኩ ገንዘብ በማተም (በማምጣት) መንግሥት ከአቅሙ በላይ እንዲሆን አድርጎታል።

# ስፖርት





## ታላቁ ሩጫ የበጎነት መገለጫ

**ዓስማየሁ ግዛው**

ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የጎዳና 10 ኪሎ ሜትር የሩጫ ውድድር መካሄድ ከጀመረ እነሆ 23 ዓመታትን አስቆጥሯል:: በእነዚህ ዓመታት ከፍተኛ ተሳታፊን በማፍራትና ከትልልቅ ዓለም አቀፍ የጎዳና ውድድሮች ተርታ መሰለፍም ችሏል:: ውድድሩ ከተጀመረበት ወቅት አንስቶ ከውድድር ባሻገር በርካታ በጎ ምግባሮችን በማድረግ ለበርካታ ወገኖች አለኝታነቱን አሳይቷል:: የዘንድሮ ውድድሩን ሲያካሂድም ይሄንኑ አጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል:: ከዋናው የጎዳና ሩጫ ጎን የሚካሄደው የሕፃናት ውድድርም ይሄንኑ ዓላማ አንግቦ ይካሄዳል::

የዚህ ዓመት ሌሎችን ለመርዳት እሮጣለሁ የገቢ ማሰባሰቢያ ዘመቻ በይፋ የተጀመረ ሲሆን ከሕፃናቶች ውድድር የሚገኘው ገቢ የፖሊዮ በሽታን ለመጥፋትና በተለያዩ ችግሮች ውስጥ የሚገኙ ሴቶች፣ ሕፃናትና አካል ጉዳተኞችን ለመርዳት እንደሚውል ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ አስታውቋል። ታላቁ ሩጫ ከሚያካሂዳቸው ውድድሮች ውስጥ አንዱ የሆነው የሕፃናት ውድድር ፖሊዮን ለማጥፋት እና ለእሷ ቢዝነስ (for her business) በሚል መሪ ሃሳብ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ያሉትን ሕፃናት፣ ሴቶችና አካልጉዳተኞችን ማገዝ ዓላማ በማድረግ ይካሄዳል።

ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ዓለምአቀፍ የጎዳና 10 ኪሎ ሜትር የሩጫ ውድድር በየዓመቱ የተለያዩ ዓላማና መልዕክቶችን በመያዝ ከሩጫው ጎን ለጎን በብዙ ችግርና መከራ ውስጥ ያሉ ወገኖችን ለመርዳት የሚያደርገውን እገዛ ከጀመረ 18 ዓመታትን አስቆጥሯል። የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ አካል የሆነው የ2016 ዓ.ም ፖሊዮን ጨርሰን እናጥፋ የሕፃናት ሩጫ እና ሌሎችን ለመርዳት እሮጣለሁ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም በችግር ውስጥ ያሉትን በርካታ ሴቶች፣ ሕፃናትና አካል ጉዳተኞችን ተደራሽ ያደርጋል። በዋናው ሩጫ ዋዜማ የሚካሄደው የሕፃናት ውድድር ‹‹በጋራ ፖሊዮን እናጥፋ›› እና ‹‹ክትባት ለሁሉም ሕፃናት›› በሚል ሃሳብ ይካሄዳል። ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ የ2016 ዓ.ም ውድድር ኅዳር 9 ቀን 2016 ዓ.ም የሚካሄድ ሲሆን፤ የሕፃናት ውድድር ኅዳር 8 ቀን 2016 ዓ.ም ይካሄዳል።

በዚህ ፖሊዮን ጨርሰን እናጥፋና ለሷ ቢዝነስ (for her business) በሚለው የሕፃናት ውድድር ላይ 3 ሺ 500 ዕድሜያቸው ከ11 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት ይሳተፉበታልም ተብሏል:: ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ የ2016 ዓ.ም ምዝገባ ከተጀመረ ወራትን ያስቆጠረ ሲሆን የሕፃናት ውድድሩ ምዝገባ በዛሬው ዕለት መስከረም 28/2016 ዓ.ም የሚጀመር ይሆናል:: ለሩጫው የሚመዘገቡት ተሳተፊዎች 360 ብር በመክፈል መመዝገብ እንደሚችሉም ተጠቅሷል::

የዚህ ዓመት ሌሎችን ለመርዳት ሮጣለሁ የገቢ ማሰባሰቢያ ውድድር ዘመቻ ከሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከተባበሩት መንግሥታት የልማት ኤጀንሲ ጋር በመተባበር በአማራ፣ ትግራይና አፋር ክልል በጦርነቱ ምክንያት ከሥራቸው የተፈናቀሉ አንድ ሺህ የሚሆኑ ሴቶችን መልሶ ለማቋቋም እንደሚውልም ተገልጿል። የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ሥራ አስኪያጅ ዳግማዊት አማረ ታላቁ ሩጫ በጎ ነገር ላይ የሚሠሩ ድርጅቶችን በማስተባበር የገቢ ማሰባሰቢያ ሲደረግ እንደቆየ ገልጻለች:: በዚህም እስከ ዛሬ ከ20 ሚሊዮን ብር በላይ ተሰብስቧል:: በተጨማሪም በአንድ ወቅት ከዚሁ ውድድር በተገኘው ገንዘብ ትምህርት ቤት መገንባቱንም አስታውሳለች:: አንድ ሺ ሴቶችን ተጠቃሚ በሚያደርገው ለሷ ቢዝነስ በሚለው መርሐ ግብር ደግሞ አንድ ሺ ሴቶችን ለማገዝና መልሶ ለማቋቋም እንደታቀደም ተጠቁሟል:: በዚህ የገቢ ማሰባሰቢያ የዘመቻ ሩጫም 500 ሺ ዶላር ለመሰብሰብ ታቅዷል። ለእያንዳንዱ ግለሰብም 500 ዶላር ድጋፍ በማድረግ የመልሶ ማቋቋም ሥራ ይሠራል::

እንደ ሥራ አስኪያጇ አስተያየት ታላቁ ሩጫ በአንድ ቀን ውድድር ብዙ ሰው የሚያሰባስብ በመሆኑ እና ብዙ ሚሊዮን ተመልካች ያለው በመሆኑ እንደዚህ ዓይነት በጎ ምግባሮች ለመሥራት ቀላል ይሆናል:: በ2015 ዓ.ም በተደረገው ጥናት ኢትዮጵያ ወደ 1 ሚሊዮን ዶላር እንድታገኝ አድርጓል:: ይህም የውጭ ምንዛሬ ፍሰትን በማሳደግ ሀገሪቷ ያለባትን የምንዛሬ ክፍተት ይሸፍናል:: ኅብረተሰቡን ከማገዝ፣ ቱሪዝምን ከማስፋፋትና የምንዛሬ ፍሰትን ከማሳደግ በተጨማሪ ብዙ ተዘርዝረው የማያልቁ ሥራዎችን ማበርከት እንደቻለም ሥራ አስኪያጇ ታስረዳለች:: ይህ ለበጎነት የሚደረገው ሩጫ ሲጀመር 88 ሺ ብር ብቻ ነበር የተሰበሰበው:: ለዚህም ብዙ ሥራዎችን መሥራትና ግንዛቤ መፍጠር አስፈልጎ ነበር:: አሁን ግን ካስቆጠረው ዕድሜና ቆይታ አንጻር ለውጦች አሉ::

ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ 10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ሩጫ በአፍሪካ ከሚካሄዱ የጎዳና ውድድሮች ሁሉ ቀዳሚና ትልቅ ሲሆን ኢትዮጵያን በዓለም መድረክ ማስጠራት የቻሉትን ኮከቦች በማፍራት ተጠቃሽ ነው። በተሳታፊ ቁጥርና በዓለም ከሚገኙት ታላላቅ የጎዳና ላይ ውድድሮች አንዱ የሆነው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ በርካታ ተሳታፊዎች ይካፈሉበታል።